Institute of Development and Education for Africa (IDEA), Inc.
*የአፍሪቃ የልማትና ትምህርት ተቋም* (*አልትተ*) August 5 2010

# ሰሞኑን ካነበብኳቸው ሦስት መጻሕፍት

## ገላውዴዎስ ኣርኣያ

1. ምስክርነት፡ በባለሥልጣናቱ አንደበት ሻ/ል ተስፋዬ ርስቴ
2. የደራሲው ማስታወሻ   ተስፋዬ ገብረአብ
3. ነጻነትና እና ጻኘነት በኢትዮጵያ ስየ አብርሃ

## ምስክርነት ተስፋዬ ርስቴ ግንቦት 2001 አሳታሚ፡ አልተጠቀሰም

*ምስክርነት ከሞላ ጎደል ለኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክና የፖለቲካ አመለካከት አስተዋጽኦ ይኖረዋል፣ በተለይም በደርግ ጊዜ የተካሄዱትን ትግሎችና የልዩ ልዩ ፓርቲዎች አሰላለፍና ተግባር ሕቡእ የነበረውን በገሃድ ያስቀምጠዋል። ይኸንንም ማድረግ የበቃው ደራሲው በርካታ ኢትዮጵያውያን በየካቲት 66 አብዮትና በኋላ በኢትዮጵያ ፖለቲክ የተሳተፉ፡ የመሩ፡ የታሠሩ፡ የተወገዙ፡ ወይም ከመዓቱ የተረፉትን በመጠየቅ ያጠናቀራቸውን መረጃዎች፡ ግንዛቤዎችና፡ ትርጉሞች፣ እርሱም በሚመስለው የእደገፊና ፍች እየሰጠ በመጽሐፍ መልክ ለማውጣት መቻሉ ነው።*

*በገጽ IX የ ኮ/ል ፍስሐ ደስታ አመለካከት መሰረት በማድረግ፡ ደራሲው "የሌሎች ፍላጎት አራማጁ ሆኖ በአገሩና በወገኖቹ ላይ እልቂት አድራሽና ለእልቂት ምክንያት የሆነው ለተገንጣዮች ስትራጂስቶችም ዓላማ አስፈጻሚ የነበረው የኢሕአፓ መሪዎቹ ቀዳሚ ተጠያቂ መሆን የሚገባቸው ይመስለኛል" በማለት ኢሕአፓን ይወነጅልና በገጽ 77 ደግሞ ፓርቲው በነሞገስ ወ/ሚካኤልና ዓለማየሁ ኃይሌ ወደ ደርግ በመሥረግ "ሥልጣን ባቋራጭ ለመንጠቅ" እቅድ እንደነበራቸው ይገልጻል። በተጨማሪም ደራሲው በኢሕአፓ ላይ ከባድ ክስ ያቀረበው ነገር ቢኖር በገጽ 97 የተመለከተውን ነው። እንዲህም ይላል፦*

*"ኢሕአፓ ደርግንና መኤሶን ለማጥፋት ከወራሪው የዝያድ ባሬ ጦር ጋር ተሰልፎ የኢትዮጵያን ሠራዊት ለመበተን ከውስጡ ሆኖ መሪዎቹን ገደለ። ከገንጣይ አስገንጣዮች ጋር ተሰልፎ ኢትዮጵያን ለማጥፋት ታገለ።"*

*ደራሲው አስተያየቱን በፈለገው መንገድ ለመግለጽ መብቱ የተጠበቀ ነው። ነገር ግን በኢሕአፓ ላይ ያለው አመለካከት እጅግ የተምታታና የተዛባ ከመሆኑም በላይ አበው እንደሚሉትም 'የወደቀ ዛፍ መጥረቢያ ይበዛበታል' ይመስላል። አላዛ ባሁኑ*

ጊዜ ኢ.ሕአፓ የመንግሥት ሥልጣን ቢጨብጥ ኖሮ ደራሲው እንዲህ ዓይነት ክስ በፓርቲው ላይ አይሰነዝርም ነበር።

በነገራችን ላይ፡ እኔ ኢ.ሕአፓን በቅርቡ የማውቀውና ያቀፍኩት ድርጅት ነበር፣ እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ድርጅት (በዓለም አቀፍ ደረጃም ሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች) ጠንካራና ደካመ ጎኖች ነበሩት፣ የጻድቀናትና የመላእክት ድርጅት አይደለምና። ስለሆነም በ1995 እአአ በጻፍኩት መጽሐፍ (ETHIOPIA: The Political Economy of Transition) አራተኛው ምዕራፍ ስለ 'ኢ.ሕአፓና የኢትዮጵያ የግራ ኃይሎች' ሆኖ ፓርቲው ያከናወናቸው መልካም ስራዎችና ያሳያቸው ድክመቶች በግልጽ አስቀምጪዋለሁ።

ሻ/ል ተስፋዬ እንደዘገበው ከሆነ ምናልባት አንዳንድ ግለሰቦች ከሰሜን አመሪካና አውሮጳ መጥተው ፓርቲው ውስጥ የተቀላቀሉ ሰርጎ ገቦች ሊኖሩ ይችላሉ፣ ግን ፓርቲው ከናካቴው የምዕራብ ቅጥረኛ ወይም ትክል አድርጎ ማቅረቡ እጅግ በጣም የተሳሳተ ነው። ኢ.ሕአፓ በጣም ብዙ አገር ወዳድ አርበኞች ያፈራና ጀግኖች የተሰዉበት ድርጅት ነው። በተጨማሪም የኢትዮጵያ ምልአተ ሕዝብ ድጋፍ ያገኘና ልዩ ልዩ ብሔሮችና ብሔረሰቦች (ኤርትራውያን ሳይቀሩ) የተሰለፉበት ፓርቲ ነበር። ለዚህም ይመስለኛል ደራሲው ያነጋገራቸው ሁለት ሰዎች ማለትም አበራ አጋ እና ሻ/ል ለገሠ አስፋው (ገጽ 93-94) እንኳ "ኢ.ሕአፓ በጊዜው ከፍተኛ የሕዝብ ድጋፍ" ማግኘቱና ከመኤሶን ባላይ ፓርቲው በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት እንደነበራው ቃላቸውን የሰጡት። ኢ.ሕአፓ የሕዝብ ድጋፍ እንደነበረው ዓለም ጠቅላላ የሚያውቀው ነው፣ ድጋፉ ግን በጸሎት የመጣ ችሮታ ሳይሆን ፓርቲው ከሕዝብ ጋር ተቆራኝቶ ስለነበረና በጠቅላላ ኢትዮጵያም ሥራውን (በሕቡእ) ማከናወን መቻሉ ነው።

ሆኖም ግን ከፍ ብየ እንደጠቀስኩት ኢ.ሕአፓ ድክመቶችም ነበሩበት። ግዙፍ የፓርቲ ክንውኖች በከተማ ማድረጉ፣ ለሠራዊቱ ለኢ.ሕአሠ አስፈላጊውን ትኩረት ያለመስጠቱ፣ ከሜኤሶን ጋር በነበረው ልዩነት ከሰላማዊ የእርቅ ድርድር ይልቅ በጠበንጃ ለመፍታት መወሰኑ ወዘተ ከነዚህና ሌሎች የመዋቅርና የአሰራር ድክመቶች በስተቀረ በወንጀልኘት የሚጠየቅ አይመስለኝም። በተቃራኒ ደራሲው በገጽ 80 ዶ/ር ወርቁን በመጥቀስ ያስቀመጠውን ሐተታ ርትዓዊ ይመስለኛል፡- "ሜኤሶንና ኢ.ሕአፓ ለኢትየጵያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትልቅ የዕድገትና የመሻሻል ተስፋ ነበሩ፡ ነገር ግን በብስለት ጉድለት እርስ በርስ ተመታተው በመጨረሻ...በደርግ...ተመቱ"። 'የብስለት ጉድለት' ብቻ በቂና አሳማኝ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡ ምክንያቱም ለብስለቱና ለእውቀቱ'ማ በሁለቱ ድርጅቶች ዘንድ እጅግ በጣም የተማሩ ሰዎች ስለነበሩባቸው በዛ ረገድ እጥረት ሊኖር አይችልም ነበር። አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ምሁራን እንደሚሉት ከሆነ ግን ሜኤሶንና ኢ.ሕአፓን ያጠፋፋ ስውር ኃይል ሳይኖር አይቀርም ነው።

የተሰወረ ጉዳይ ወይም ስውር ኃይል ሊኖር ላይኖር ይችላል። ደራሲው በገጽ X ያመለከተውን ግን አሁንም ቢሆን የሚያጠራጥርና የሚያጠያይቅ ነው፡- "ከመከላከያ ቅጥር ግቢ ሳይወጡ የምድር ጦር፡ የአየር ኃይልና፡ የፖሊስ ሠራዊት አዛዦችና ታዋቂ ከፍተኛ ጀነራሎች ሞቱ...አሥራ ሁለት ጀ/ል መኰንኖች ከፕረዚደንት ቢሮ

ዙርያ በነበሩ ሰዎች በተላለፈ 'የፍርድ ብይን' በጀ/ል አሥራት ብሩ አንደበት 'በችሎት' ላይ ተነበበና የሞት ቅጣት በቅጽበት ተፈጸመባቸው።" እንዲህ ዓይነት አገዳደል ደርግ እሰከሚወድቅ ድረስ ይካሄድ ነበር። ታድያ እነዚህን ጀነራሎች የሚገድል ያልታወቀ ስውር ኃይል ኖሯል ብለን ነው የምንጠይቀው ወይስ ደርግ ደንቃራና ልበቢስ ስለነበረ ነው የገዛ ራሱ ምርጥ መኰንኖች የጨረሰው?

በገጽ 40 ደራሲው "አፄ ኃይለሥላሴ ኢትዮጵያን ወደ ዘመናዊ ሥልጣኔ ለማስገባት አንፃራዊ በሆነ መልኩ ጥረት አድረገዋል...ቴዎድሮስ ያለሙትን ዳግማዊ ምንሊክ የጀመሩትን ዘመናዊ ሥልጣኔ ለኢትዮጵያ ለማስገኘት ደክመዋል ለፍተዋል።" ይህ በመሰረቱ ትክክል ሆኖ ትንሽ ግን የተጋነነ ነው። አፄ ኃይለሥላሴ በነበራቸው ዕድልና ረገርም የሥልጣን ዘመን (44 ዓመት ማለት የአሥር የአመሪካን ፕረዚደንቶች የሥልጣን ዘመን ማለት ነው) ኢትዮጵያን ከጨለማ አውጥተው ብርሃን ማልበስ ይችሉ ነበር፣ ግን አላደረጉትም።

ሌላ የሚገርም ነገር ግን ጸሐፊው ዘመናይ የኢትዮጵያ ነገስታት ሁሉንም ጠቅሶ አፄ የሓንስን መዝለሉ ነው። ከዚህ ቀደም ማሞ ሙጬ ከደቸሸለ አማርኛ ፕሮግራም ባደረገው ቃለመጠይቅ ነገሥታቱን ጠቅሶ (ልጅ እያሱን ሳይቀር) የሐንስን በመርሳቱ ወቅሼው ነበር። በተመሳሳይ መልኩ አምሃ ዳኘ (የቅንጅት አባል) በአንድ ጽሑፉ አፄ ዮሐንስን ሳይጠቅስ በማለፉ ነቀፌታ ሰንዝሬበት ነበር። በጣም ደስ የሚል ነገር ቢኖርና 'የተማረ ይግደለኝ' የሚያሰኘው ግን ማሞ ሙጬ እና አምሃ ዳኘ ከኔ ጋር ባደረጉት የኤለክትሮኒክ ደብዳቤ ልውውጥ 'አፄ የሐንስን ሆን ብለው ላለመጥቀስ ፈልገው ሳይሆን በመዘንጋት እንደሆነና እንድያውም ለንጉሠ ነገሥቱ ታላቅ ክብር እንዳላቸው' አረጋግጠውኛል። ስለሆነም እኔም ለነሱ ከበሬታ እንዳለኝ ልገልጽላቸው እወዳለሁ። ሻ/ል ተስፋዬ ርስቴም በመዘንጋት እንጂ የታላቁ የኢትዮጵያ መሪ ስም ላለመጥቀስ እንዳልሆነ ይገባኛል። እንድያውም በገጽ 300 ደራሲው "የሐንስ ከድርቡሽ ጋር በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ ለአገር ክብርና ኩራት መተማ ወድቀዋል" ይላል። ይኸን ነገር እግሬ መንገዴን ያነሳሁት የትግራይ ተወላጅ ስለሆንኩና ስለከነከነኝ ሳይሆን በኢትዮጵያዊነቴ ስለምኮራና የኢትዮጵያም አጀንደ በቅድምያ ስለማራምድ ነው። ለኢትዮጵያ እንቆማለን ካልን ደግሞ ለጠቅላላ ኢትዮጵያ ነው መቆም ያለብን። ለምሳሌ ነገሥታቱን የምናነሳ ከሆነ የካፋ፡ የጦና፡ የጅማ፡ ነገሥታትና የሐረር ኢሚሮችም ጭምር ማንሳት ይኖርብናል።

ለእኛ ኢትዮጵያውያን የሚያዋጣን ነገር ቢኖር በጎጥና ብሔር ፖለቲካ ሳንወሰን ኢትዮጵያ-አቀፍ አጀንዳ ማቀፍና ማስቀደም ስንችል ነው። ከዚህ ቀደም በተለያዩ ጽሑፎቼ እንዳመለከትኩት አንድ ኢትዮጵያዊ በጋራ መለያችን 'ኢትዮጵያዊ' ተብሎ ነው መጠራት ያለበት እንጂ 'ጉራጌ' 'ሲዳማ' 'ትግራይ' 'አማራ' 'ኦሮሞ' ወዘተ ተብሎ መገለጽ የለበትም። ከዚህ አንጻር ደራሲው በገጽ 22 እና 23 መሃከል በሰንጠረዥ ውስጥ የተጠቀሰዩትን የደርግ አባላት ስማቸውና ማዕርጋቸው ብቻ ሳይሆን ብሔርነታቸውም ጭምር ጠቅሷል፣ ለምሳሌ ፍስሐ ደስታ (ትግሬ)፡ ግርማ ቡርቃ (ኦሮሞ)፡ ሞገሥ ወ/ሚካኤል (ሐማሴን)። የመጨረሳው 'ኤርትራ' መሆን ነበረበት፡ መጥቀሱ ካልቀረ። ቅድም እንደጠቀስኩት ግን የብሔርና ጎጥ ነገር ከናካቴው ማስቀረት ያለብን ጉዳይ ነው፣ የብሔሮችና ብሔረሰቦች ጥናትና ምርምር

ማድረግ ካልፈለግን በስተቀረ። ይኸም ቢሆን በበርካታ ባህሎቻችን ላይ ተንተርሰን አንድነትን ለማጐልመስ ለምናደርገው ጥረት መሆን አለበት።

ከገጽ 49 እስከ 54 የአማን ዓንዶምና የመንግሥቱ ኃይለማርያም የፖለቲካ አቋም ልዩነቶች ተተንትኗል። መንግሥቱ የኤርትራን ጉዳይ በኃይል መፈታት አለበት ሲል አማን ግን የሰላሙን መንገድ ነበር ያራመዱት። በኤርትራ እየተዘዋወሩም ለሕዝብ መግለጫ ለመስጠታቸው የነመንግሥቱ ቡድን አልወደደውም፣ እንድያውም “ኤርትራ ራሷን የቻለች አገር ናት… ብለዋል” በማለትም እነ መንግሥቱ አማን ዓንዶምን ኮንነዋል። ደርግ ኣላወቀውም እንጂ የአማን የሰላም ስትራተጂ ነበር ለኤርትራ ታጣቂ ኃይሎች አደገኛ ሊሆን ይችል የነበረው። በአንጻሩ የደርግ የኤርትራን ችግር/ጥያቄ በጦርነት መፍታት መወሰኑ ለኤርትራ ነጻ አውጪ ግንባሮች ያልታሰበ ስጦታ ወይም ገጸ በረከት አግኝተዋል ማለት ይቻላል። ደንቃራው የደርግ ቡድን ጀ/ል አማንን በኤርትራዊነታቸው ከሰሳቸው እንጂ እሳቸው ያሉት ግን “ከማናቸውም ይበልጥ ለኢትዮጵያ መስዋእትነት ከፍያለሁ ኢትዮጵያውኔቴን ማንም እንዲጠይቀው አልፈቅድም” ነው (ገጽ 55)።

ከገጽ 63 እስከ 85 በደርግ የተረሸኑትን 60 ኢትዮጵያውያን ስም ዝርዝር አለ። ከነዚሁ አብዛኞቹ በእስራት ጊዚያቸውን ካሳላፉ በኃላ ይፈታሉ የሚል እምነት ነበራቸው። አንዳንዱ ደግሞ እንኳንስ ሊገደሉ የሚታሠሩም አልመሰላቸውም ነበር፣ ለምሳሌ ሪር አድሚራል እሰክንድር ደስታ ከጅቡቲ ተመልሰው ነበር ወደ አዲስ አበባ የመጡት። ደርግም የጀ/ል አማን ሚካኤል ዓንዶም ያልተጠበቀ ሞት ስላስደነገጠው ሳይሆን አይቀርም ለሸፋን ያህል እነዚህን የድሮ ሹማምንት ያጨደው፣ ይህ ባይሆን ኖሮ ደግሞ እንደነ ሌ/ጀ/ል ኢሳያስ ገብረሥላሴ ከሆስፒታል ከተኙበት አልጋ ተወስደው አይረሸኑም ነበር።

በገጽ 67 “ከሐማሴን ታጣቂዎች ጋር ሰላም ለማምጣት የተጀመረው ጥረት ፍሬያማነት ከጀ/ል አማን ጋር አብሮ ተገደለ” የሚለውን ትክክል አባባል ሆኖ፡ ከፍ ብየ ለማስገንዘብ እንደመኮርኩት፡ ‘ሐማሴን’ የሚለውን ዘይቤ ግን የተሳሳተ ነው፣ ‘ከኤርትራ ታጣቂዎች’ መሆን ነበረበት። በጥንት ጊዜ፣ ኤርትራ ከመፈጠሯ በፊት፡ አገሩ ምድሪ ባሕሪ ወይም መረብ ምላሽ አንዳንዴም ሓማሴን ተብሎ ይታወቅ ነበር፣ ኤርትራ በጣልያን ቅኝ ግዛት ከተፈጠረች ወዲህ ግን ‘ሓማሴን’ ያንድ አውራጃ ስም ሆኖ ቀርቷል።

በገጽ 68 “ሻ/መንግሥቱ የሰውን ሐሳብ ተቀብለው የራሳቸው የማድረግ ከፍተኛ ችሎታ ኣላቸው ይባላል” የሚለውን አጠቃላይ የኢትዮጵያውያን ሊሂቃን ስነልቦና (ወይም በራስ ያለመተማመን) የሚያንጸባርቅ ነው። ድሮ አፄ ኃይለሥላሴ ‘ኃይማኖት የግል ፣ አገር ግን የጋራ ነው’ ያሉትን የሳቸው ሳይሆን የልጅ እያሱ መኖሩን ‘ልጅ እያሱና አፄ ኃይለሥላሴ’ በሚል ጽሑፌ ጠቅሼዋለሁ፡ ማንበብ ከፈለጉ www.africanidea.org/Doc3.pdf ይጎብኙ። ሻ/መንግሥቱ ‘አብዮት የራት ግብዣ አይደለም’ ሲል የራሱ ቢሂል አስመስሎ ነበር የሚያቀርበው፣ ‘ማኦ ዘዱንግ እንዳለው’ ሲል ሰምቼው ኣላውቅም። አሁንም ቢሆን የኢህአዴግ አመራሮች የራሳቸውን ያልሆነ ሐሳብ/አባባል/ዘይቤ የነሱ እንደሆነ አድርገው ነው የሚያቀርቡት። አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ሊሂቃንና ምሁራን በተመሳሳይ መልኩ

ያላፈለቁትን ፍሬ ነገር እንደ የራሳቸው (ምንጩን ሳይጠቅሱ) አድርገው ያስቀምጡታል። ለምሳሌ 'ለኢትዮጵያ የሚበጅ ስትራተጂ መቀየስ የሁላችን ኃላፊነት ነው' በሚል ርእስ በጻፍኩት ጽሑፍ ላይ 'በአንድ ብሔር መወለድ ያጋጣሚ ጉዳይ መሆኑንና ብሔርን መምረጥ እንደማይቻል' ብየ ያልኩትን ብያንስ ብያንስ ሦስት ግለሰቦች እነሱ እንዳፈለቁት አድርገው አቅርበውታል። እኔ ለነገሩ ቅር አልሰኝም፣ ግን የማንኛውም ጥናታዊ ጽሑፍ ምንጭ መጥቀስ ግዴታና ሓላፊነት ይጠበቅብናል።

ሌላው የኢትዮጵያውያን ኋላቀር የሥነልቦና አመለካከት የሚያንጸባርቅ በገጽ 84 የተጠቀሰውን የዓለማየሁ ኃይሌ አንደበት ነው፦ 'ይህ ባርያ በአገር፡ በሕዝብና በኛ ተጫወተ' ያለውን መንግሥቱ ኃይለማርያምን የሚመለከት ነው። የዚሁ ኋላቀር አስተሳሰብ የሚደግፍም በገጽ 128 ተገልጿል። መንግሥቱ ኃ/ማርያም "በወጣትነት ጊዜያቸው ደብረማርቆስ ሲኖሩ ብዙ መጥፎ ትዝታ ቋጥረዋል። መልኩ ጠቆር፣ ፀጉሩ ከርደድ በተለይም ከንፈሩ ወፈርና ለጠጥ ያለን ሰው ጉጀሞች "ባርያ" ይላሉ፡ ይንቃሉ። ሲሳደቡም " ቅሪንዲላ ባርያ፡ ውርንጭላ፡ መሸጦ፡ የወጨፎ ልዋጭ" በማለት ነው።" በገጽ 210 እንደተመለከተውም "ባለሥልጣናቱ 'ጠቋሬ' እያሉ ነበር ፕሪዚደንቱን የሚጠሯቸው..."

የአስተሳሰብ ለውጥ ካልቀደመ በስተቀረ ደግሞ ስኬታማ የልማት ጎዳና ለመቀየስና በግብር ለመተርጎም እጅግ በጣም አዳጋች ሊሆን ነው። ባንድ በኩል፡ ምንም እንኳ መንግሥቱ ኃ/ማርያም በጭካኔውና በሰራቸው ወንጀሎች ብንኮንነውም፡ የኋላቀር አመለካከት ለመምታት ግን እንኳን ወደ ሥልጣን መጣ የሚያሰኝ ነው። የመልክ ጉዳይ ካስተሳሰብና ከባህል ጋር በረቀቀ መልኩ የተያያዘ ስለሆነ በቀላሉ ከኋላቀር አመለካከት ነጻ መሆን አይቻልም እንጂ፡ መሆን ያለበት ሁሉም ሰው (ኢትዮጵያዊ) ቆንጆ ነው ብሎ ማሰብ ነው። ጠለቅ ብለን ካሰብነበት ደግሞ ጥቁሩ፡ ጠይሙ፡ የቀይ ዳማው፡ ባለ ሉጫ ጸጉር፡ ባለ ከርዳዳ ጸጉር፡ ባለ ደፍጣጣ አፍንጫ፡ ባለ ሰልካካ አፍንጫ ሁሉም ቆንጆ ናቸው።

በገጽ 95 ተስፋዬ መኰንን "በጥቁር አፍሪካ ታይቶ የማይታወቅ ሕዝባዊ አብዮት በኢትዮጵያ ውስጥ ተካሂዷል" ያሉትን የተጋነነና ከእውነት የራቀ ነው። በእርግጥ የየካቲት 66 አብዮት በመጠኑም ቢሆን በአንዳንድ ኅብረተሰባዊ መስኮች ላይ ሥር ነቀል ለውጥ አምጥቷል ማለት ያቻላል፣ 'በጥቁር አፍሪካ ታይቶ የማይታወቅ' ብሎ ማለት ግን የአንጎላ፡ የሞዛምቢክ፡ የጊኒ ቢሳው (እንዳሁኑ አያድርገውና) እና የአልጀርያን (ጥቁር አይደለም ካልተባለ በስተቀር) አብዮቶች መዘንጋት ነው የሚሆነው። እነዚህ አፍሪቃ አገሮች ምንም እንኳ የኢትዮጵያ ዓይነቱ ማሕበራዊ አብዮት ባያካሂዱም የቅኝ ግዛት ሥርዓቶችን በመደምሰስ እና በአፍሪቃውያን የሚመራ አዲስ የፖለቲካ ሥርዓት መገንባታቸው ግን አብዮት አካሂዷል ማለት ይቻላል። በሰላማዊ መንገድ ሆኖ ነጻነት የተቀዳጀችና ማሕበራዊ አብዮት ያከሄደች ደግሞ ታንዛንያ እንደ አብነት የምትጠቀስ ነች።

በገጽ 100 ደራሲው ከክፍሉ ታደሰ መጽሐፍ 'ያ ትውልድ' በመጥቀስ "የተሓኤ ቡድን በራሱ አነሳሽነት ለኢህአሠ ማማርያዎችን ከመስጠቱ አልፎ ለኢሕአፓ ሠራዊት አባላት ወታደራዊ ሥልጠና በማድረግ ረድቷል" የሚለውን የተሳሳተ ነው።

እኔ እስከማውቀው ድረስ በተሓኤ የሰለጠኑ የኢሕአሠ የሰራዊት አባላት የሉም፣ በህግሓኤ (ሻዕብያ) ግን ሳሕል ውስጥ የሰለጠኑ ነበሩ። ተሓኤ (ጀብሃ) ደግሞ ለኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት (ኢህአሠ) የመሳርያ እርዳታ ያደረገ አይመስለኝም። በተቃራኒ ግን ለኢህአሠ ከውጭ የተላከውን መሳርያ በባርካ (ተሓኤ የሚቆጣጠረው ምዕራብ ኤርትራ) በኩል ወደ አሲምባ ይተላለፍ ስለነበር ከልዩ ልዩ መሣርያዎች የበልጂክ ጠበንጃዎች በማስቀረት (በመንጠቅ) ተሓኤ ንብረትነቱ እንዲሆን አድርጎታል።

በገጽ 102 ደራሲው በከፍተኛ ወንጀል ሊያስጠይቅ የሚችል ሐተታ ሰንዝሯል፦ "ጌታቸው ማሩን መስፍን ሐርር መንገድ/በላይ ዘለቀ በሸመቁበት ቦታ ገድለው ራሱን፡ እጅ እግሮቹንና ሌላውን አካሉን ለየብቻ ቆርጠው በጆንያ ከትተው ክፍሉ ታደሰና ተስፋዬ ደበሳይ አውጥተው ሊጥሉት (ለተገንጣይ ስትራጂስቶች ሲሉ) ሲሰናዱ ጌታቸው ሽበሺ የመራው ጦር ደርሶባቸው የተቆራረጠውን አስከሬን ጥለው አምልጠዋል።" ይህ አረሜናዊ ግፍ ተደርጎ ከሆነ በህይወት ያለውን ክፍሉ ታደሰ መመለስ አለበት፣ ተሰፋዬ ደበሳይ ሞቷልና። በዚሁም ገጽ "ተሰፋዬ ደበሳይ በንግሥት አዳነ ጠቋሚነት ጠቅላይ ፖስታ ቤት አከባቢ ሊያዝ ሲል አምልጦ ከአምባሳደር የመጨረሻ ፎቅ ተወርውሮ ራሱን ገደለ..." እውነትነት ያለው ሆኖ፡ ምናልባት ካልተሳሳትኩና ካልዘነጋሁ በስተቀር ግን፡ ዶ/ር ተስፋይ ተወርውሮ ራሱን የገደለው ከ ኪዳኔ በየነ ህንጻ ነው።

በገጽ 212 በከሸፈው የግንቦት 8 1981 መፈንቅለ መንግሥት የተሳተፉ የጀነራሎች ስሞች ተጠቅሷል፣ ግን ያልተጠቀሱ ግለሰቦች በሃገር ውስጥም ከውጭም ለሴራው ድጋፍ በመስጠትና ስትራተጂ በመቀየስ ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ ሳይኖሩ አይቀርም።

መፈንቅለ መንግሥቱ ከከሸፈ በኋላ ግን "የሚያሳዝነው የአገዳደላቸው ጭካኔና ከግድያው በኋላ በሬሳቸው ላይ የተፈጸመው እንስሳዊና አረሜናዊ ጭካኔ ነው። የተገደሉት ጀነራሎች ዓይናቸው በሳንጃ፡ ፈርጧል እጅና እግሮቻቸው ተቆራርጧል፡ ልብሳቸው ከአስከሬኖቹ ላይ ተገፎ ሬሳ እርቃኑን እንደውሻ ሬሳ ከመንገድ ላይ ተጥሏል። በተለይም የብ/ር ታየ ባሊከር አስከሬን በራስ ገዙ ፖሊስ ዋና መምርያ ውስጥ መሬት ለመሬት ተጎትቶ ተቆራርጧል።" (ገጽ 215)።

እንዲህ ያለ አረሜንነት የሚዘገንን፡ የሚያሳዝንና፡ የሚያስፈራ ብቻ ሳይሆን እጅግ በጣም የሚያሳስብም ነው። ለመሆኑ እንዲህ ያለ ጭካኔ ከየት የመጠ ነው? በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከዚህ ቀደም ያልተከሰተ የሰው በላ ፖለቲካ ምንጩ ምን ይሁን? ይኸንን በቅጡ ጥናትና ምርምር አድርገን ዳግመኛ በታሪካችን በፍጹም እንዳይደገም የሁላችን ግዴታና ኃላፊነት መሆን አለበት።

በገጽ 236 "የግንቦት 8 1981 የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ መክሸፍ የኤርትራን መገንጠል አፋጠነ፡ እውንም አደረገ። በሰሜን ኢትዮጵያ ይካሄድ የነበረው ጦርነትም ለገንጣይ አስገንጣዮች አመችነት ባለው መልክ እንዲደመደም አስተዋጽኦ አደረገ። የሠራዊቱ መዳከምና መሪ አልባ መሆን ገሃድ ወጣ" የሚለውን ሐተታ፡

ከመጨረሻው ሐረግ በስተቀረ፡ ከነበረው የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የራቀና ሓቅነት የሌለው ነው።

የኢትዮጵያ ሠራዊት በሰሜን ግንባር (ኤርትራና ትግራይ) የተቸነፈው፡ 1) ደርግ ራሱ (ወይም በውስጡ የተሰገሰጉ ሕቡአን) ብቃት ያላቸውን ጀነራሎች እንደነ ጀ/ል ታሪኩ በመግደሉ፣ 2) የደርግ አፋኝ ቡድኖችና የቀይ ሽብር ደንቃራዎች በትግራይና በኤርትራ (በሌላ የኢትዮጵያ ክፍላተ ሃገራትም ጭምር) ወጣቱን በግፍ በገደሉ ቍጥር የተረፈው ወጣት ወደ ግንባሮቹ መቀላቀሉ፣ 3) የህወሓት (ወያኔ) ሠራዊት በደርግ ሠራዊት ላይ ከፍተኛ ጥቃት በመሰንዘር፣ በተለይም በሽሬ አካባቢ የነበረውን ኃይል በመደምሰስ የሠራዊቱ የመዋጋት ሞራል ዳሽቆት ስለነበረና፣ 4) ወያኔና ሻዕቢያ በመተባበር፡ አንዳንዴም ኃይላቸውን በማቀናጀት የኤርትራን ነጻነት እውን ማድረግ ብቻ ሳይሆን የደርግ ሠራዊት የሚበታተንበት ሁኔታ ከፈጠሩ በኋላ ኢህአዴግ ሥልጣን የሚጨብጥበት መንገድም አፋጥኖታል ማለት ይቻላል።

መንግሥቱ ኃ/ማርያምና በዙርያው የነበሩ ከፍተኛ የደርግ አመራሮች ሥልጣናቸው ያከተመ መሆኑን የተረዱት ህወሐት/ኢህአዴግ አምቦ አከባቢ እንደደረሰ ሳይሆን ህወሐት በየካቲት 1981 ከሦስተኛ አብዮታዊ ሠራዊት (የደርግ) ጋር በሽሬ እንዳሥላሴ ለአምስት ቀናት ባደረገው ፍልምያ ከፉኛ ከመታውና ከበታተነው በኋላ ነው። ከዚህ በኋላ የደርግ ዘመነ መንግሥት ድምዳሜ ተከሰተ።

በገጽ 257 እንደገና ደራሲው ለኢትዮጵያ ሠራዊት መድከም ከሜኤሶንና ኢሕአፓ ጋር ያያይዘዋል። እንዲህም ይላል፦ "የኢትዮጵያ ሠራዊት በጉያው የገንጣይ የመኢሶንና ኢሕአፓ እሳት አቅፎ በተዳከመበት ወቅት ወረራ ሲሰዘነርበት አስደንጋጭ ሁኔታ ገጠመው። በውስጡ ያሉትን ውስብስብ ችግሮች እንዳዘለ ለአገር ክብርና ለወገን መስዋዕትነት የሚከፍለውን የኢትዮጵያ ሠራዊት እንዳይዋጋ ለማድረግ 'ሶማልያ የምትዋጋ ራሷን መሬት ለማስለቀቅ ነው" /Somalia claims her own land/፣ የደርግን ዕድሜ ለማራዘም ራስህን መስዋእት አታድርግ' የሚሉ ቅስቀሳዎችን አካሄደ። በጦሩ ውስጥ የተሰገሰጉ የኢሕአፓ ነብሰ ገዳዮች መሪ መኰንኖችን በውግያ ከጀርባ ገደሉ። በተለይ በደቡብ ግንባር በባሬና በደሎ የውግያ ቦታዎች በ21ኛ እና በ28ኛ የሻለቃ ጦር አዛዥነት ቦታ ደርሰው የነበሩ የኢሕአፓ አባላት የመሯቸውን ሻለቆች ለጠላት አጋልጠው አስጭርሰዋል።" ለዚሁ በኢሕአፓ የተበተነው የሚባለው ሰነድ እርግጠኛነት አጠራጣሪ የሚያደርገው ደራሲው በግርጌ ማስታወሻ ይሁን በዋቢ መጻሕፍት ደጋፊነት መረጃ ያቀረበው የለም። ያቀረበው ነገር ቢኖር በግርጌ ማስታወሻ ቍጥር 6 ላይ "ስኳር ላሹ" የሚለውን ታምራት ላይኔን ሆኖ የድሮ ጠ/ሚኒስትሩ 'ኢትዮጵያ ሶማሊያ አሁን ለደረሰችበት መንግሥት አልባነት ተጠያቂ ናት' በማለቱ ነው። ይህ ኢሕአፓ አደረገው ከተባለው ወንጀል ጋር ምንም የሚያገናኘው ነገር የለም።

የሆኖ ሆኖ ግን ደራሲው የሚለውን ለመንደርደርያ ያህል ብንቀበለውም እንኳ ኢሕአፓ ጸረ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውን ያደረገው በደል ያለ አይመስለኝም፣ ከሰራቸው የስትራተጂ ስሕተቶችና በሰበቡም ወጣቱን ለቀይ ሽብር ሰለባነት ከማጋለጡ በስተቀር። በሱማሌ አከባቢ ወንጀል ሰርቷል ከተባለም ምናልባት ሰርጎ ገቦች ያደረጉት ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለኝ። በነገራችን ላይ በመንግሥቱ

የሚመራው የኢትዮጵያ ሠራዊት እንደ አገር ወዳድና ለሕዝብ ደሕንነት እንድሚቆረቆር አደርጎ ማቅረቡ የተሳሳተ አመለካከት ነው። ሕዝቡን የሚጨፈጭፍ መንግሥት፣ በአዋጅ 'የፍየል ወጠጤ፣ ልቡ ያበጠበት' እያለ ወጣቱን የሚያርድ መንግሥት፣ በቀይ ሽብር ተራማጅ ኃይሉን የሚደመስስ መንግሥት እንዴት ብሎ ነው አገር ወዳድ የሚሆነው፣ ሕዝብና አገር በመነጠል የተዛባና የተምታታ ርእዮተ ዓለም ካላራመድንና በመንግሥቱ ኃ/ማርያምና ባልደረቦቹ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የደረሰው አረሜንነት ከአእምሮአችን ፍቀን ለማውጣት ካልፈለግን በስተቀረ፡ የቅርቡ ታሪካችን ሁላችን የምናውቀው ነው።

All Rights Reserved. Copyright © IDEA, Inc. አልትተ ገላውዴዎስ ኣርኣያ

## የደራሲው ማስታወሻ ተስፋየ ገብረአብ ነጻነት አሳታሚ ዋሺንግቶን ዲሲ 2002

ተስፋየ ገብርአብ ከዚህ ቀደም የጋዜጠኛው ማስታወሻ በሚል ጽሑፉ አንባብያንን አስተናግዶ ነበር፣ ደራሲው ከፍተኛ የስነ ጽሑፍ ችሎታ ብቻ ሳይሆን ስጦታም አለው ማለት ይቻላል፣ አንዳንዴም በየምዕራፋቱ በድራማ መልክ ሁኔታዎችና ወቅታዊ ክንውኖችን ስለሚገልጻቸው አንባብያንን ከምዕራፍ ወደ ምዕራፍ ሳያቆሙ እንድያነቡ ያስገድዳቸዋል። አንድአንድ የደራሲው ማስታወሻ ምዕራፋት ከሞላ ጎደል የጋዜጠኛው ማስታወሻ ትረካዎችና ገለጻዎች ተቀጥያ ናቸው ማለት ይቻላል። ለምሳሌ 'የልጅነት ተራሮች' (ምዕራፍ 1)፡ 'የቀዌሳ ዓመጽ' (ምዕራፍ 2) እና 'ወርቃማ ዓመታት' (ምዕራፍ 5) የብሽፍቱ ትዝታዎች ናቸው። 'ደጋግ ሰዎች' (ምዕራፍ 24) ደግሞ እንደዚሁ 'የጋዜጠኛው ማስታወሻ' ተከታታይ ርእሰ-ነገር ሆኖ በተለይ ግን ከንያ ውስጥ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ('ከባከኑ ሰዎች') ጋር የሚመሳሰል ነው። ስለሆነም አንድ አንድ ምዕራፋት ብቻ በመምረጥ አቃቂር ለማቅረብ ተሞክሯል።

'ሁለቱ ዝሆኖች' (ምዕራፍ 3) መለስና ስየ መሆናቸው ነው። ደራሲው የሁለቱን ባህርይ አንጻራዊ በሆነ መንግድ አስቀምጧቸዋል፣ ነገር ግን ባቀራረቡ ብዙዎች አንባብያን፣ በተለይም መለስና ስየን በቅርብ የሚያውቋቸው፣ ከደራሲው ጋር ላይስማሙ ይችላሉ። መለስ ጮሌና ጭልፊት ነው፣ ስየ በአንጻሩ ገገማ ሆኖ 'ዘነዘና የዋጠ ይመስላል፡ ከመሬት ተነስቶ ቁጣው አይጣል!'፣ 'መለስ ቀጤማ ናት'፣ በአንጻሩ ስየ በቀላሉ የሚገነፍል ዓይነት ነው። ደራሲው ሁለቱን ዝሆኖች በ ቶምና ጀሪ ይመስላቸዋል፡ መለስ ብልጥ አይጥ ሲሆን ስየ ደግሞ ጅል ድመት መሆኑ ነው።

ደራሲው የሁለቱ ዝሆኖች ባህርይ በሚገልጽበት ጊዜ፣ ምንም እንኳ የሁለቱ ጥንካሬና ድክመት ለማሳየት ቢሞክርም፡ ያደላው ግን ወደ መለስ ነው። የመለስ ባህርይ በማሸብረቅ፡ የስየን በማንቋሸሽ ነው የጻፈው። ደራሲው በጀግንነቱ ለታወቀው ስየ እንኳን "በጦር ሜዳ ውሎው ብዙ አይታማም" ብሎ ነው ያለፈው። ተስፋዬ ስየን በደንብ ያወቀው አልመሰለኝም። አንድ በጣም የሚገርም ደግሞ ደራሲው ሁለቱን ዝሆኖች አስመልክቶ "የኢትዮጵያውነት ሃገራዊ ስሜት ከደማቸው ወስጥ አስወግደው ራሳቸውን ወደ 'ንፁሕ ትግራዊነት' ለውጠው..." ያለውን ነው። እንዲህ ዓይነት

ትንተና መቸም በቀላሉ መግለጹ አስቸጋሪ ነው። ብዙ ትርጉም ሊሰጥበት ይቻላል፣ ለምሳሌ 'ሁለቱ ሰዎች ጸረ-ኢትዮጵያ ናቸው'፣ 'ጠባብ ብሔርተኞች ስለሆኑ ኢትዮጵያን አያስቀድሙም'፣ 'በስመ ኢትዮጵያ እየገዙና እየመሩ ነው እንጂ ኢትዮጵያን ለማጥፋት እየቃጡ ናቸው' ወይም 'እነዚህ ዝሆኖች ከኢትዮጵያ ውጭ ፈልሰው የመጡ አስመሳዮች እንጂ እውነተኛ የኢትዮጵያ ዝሆኖች አይደሉም ('ዝሆን በድንበር አይወሰንም፣ አገር የለውም' የሚለውን ለጊዜው ትተን) ወዘተ ወዘተ

ወደድንም ጠላንም መለስና ስዬ ኢትዮጵውያን ናቸው። ኢትዮጵያውነታቸው ሳይሆን መጠየቅ ያለበት ርእዮተ ዓለማቸው፣ የሚያራምዱት የፖለቲካ መስመር፣ አገርን አስመልክቶ የሚከተሉት ፖሊሲ እና ለሕዝብና ለሃገር ይቆረቆራሉ አይቆረቆሩም ወዘተ የሚሉትን ጥያቄዎች ነው ማቅረብ ያለብን።

በምዕራፉ መጨረሻ ደራሲው ሌላ የሚገርም ነገር ያቀረበው ነገር ቢኖር ስለ መለስና ስዬ የሚስጢር ስምምነትን አስመልክቶ ነው። ተስፋዬ ገብረአብ "ስየ እና መለስ አማሮችና ኦሮሞዎች እንደበረቱባቸው አስተውሏል። የኢትዮጵያውነት መንፈስ እያቸነፈ መሄዱን አስተውለዋል። በዚህ ወቅትም መተባበር ብቻ እንደሚያዋጣቸው ያውቃሉ። ስዬ የታሰረው በስምምነት ነው ብየ አላምንም። የተፈታው ግን በስምምነት ሊሆን እንደሚችል እጠረጥራለሁ።" ይኸንን አባባል፣ ደራሲው "መረጃ አይደልም፣ ትንተና ነው" ይለናል። ትነተናው ግን 'የኢትዮጵያዊነት መንፈስ እያቸነፈ መሄዱን' ከሚለው በስተቀር የተሳሳተ ነው። ግራም ነፈሰ ቀኝ፡ አሁን ለምልዓተ ሕዝበ ኢትዮጵያ ግልጽ የሆነ ነገር ቢኖር መለስ እና ስዬ እጅግ በጣም የተራራቀ አቅጣጫ እንደተጓዙ ነው፣ የሕቡእ ቃል ኪዳን የላቸውም። ቢኖራቸውም እንደ ማንኛውም የፖለቲካ አጀንዳ ግዙፍ ልዩነቶችን አስመስክሯል፣ እንድያውም የሁለቱ ጓደኝነት እንደ ጠዋት ጤዛ በኗል። በ 2002 ምርጫ እንደታየው ደግሞ የስዬ የፖለቲካ ጎራ (አንድነት/መድረክ) የትግራይን ሕዝብ ስላነሳሳና ስላሰከተተ ኢሕአዴግ የመሃል አገር ሕዝብ ብቻ ሳይሆን የትግራይ ሕዝብም ጭምር ነበር የፈራው።

'አብዮታዊ ኦርቶዶክስ' (ምዕራፍ 4) የአንድ ዲያቆን (ከመስቀል ወደ ጠበንጃ የተሸጋገረ) ታሪክ ነው። የዲያቆኑ ስም በርሀ ነው፣ የቅጽል ስሙ ደግሞ 'ጉማ እግሩ' ነው። የቅጽል ስሙን "ያገኘው ለስልጠና ኤርትራ በነበረባቸው በእነዝያ የመደጋገፍ ዘመናት እንደነበር ይነገራል። 'መትረየስ ተሸክሞ የናቅፋን ተራሮች እንደ ወፍ በርሮባቸዋል' ይላሉ አብረውት በቀይ ኮከብ ዘመቻ የተካፈሉ።" (ገጽ 77) ደራሲው ዲያቆኑን ከመውደዱ በላይ ግእዝ የመማር አጋጣሚነትን ተጠቅሞበታል። ዲያቆኑም የተማረ ባይሆንም ቅሉ የማሰተማር ጉጉነት እንዳለው ከደራሲው አቀራረብ መረዳት ይቻላል።

ሌላ በዚሁ ምዕራፍ መልእክት ያለው ቊምነገር ቢኖር የኢትዮጵያ ሕዝብ በቅጡ መረዳት ያልቻለው ርእዮተዓለማዊ ጽንሰሓሶቦችን አስመልክቶ ነው። ጉማ እግሩ "አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚባለው ነገር ወደ ድርጅታችን ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ እየጠየቅሁ ነበር። የሚሰጡኝን መልስ ጆሮየን ተክየ፣ ቀልቤን ሰብስቤ አዳመጥኩ። ምንም ነገር ሊገባኝ ሳይችል ቀረ" ይላል። (ገጽ 79) 'አንተ ምኑ ነው ያልገባህ' ብሎ ደራሲው ሲጠይቀው ደግሞ፡ 'ቃሉ ራሱ አልገባኝም' ብሎ መለሰ።

የ'አብዮታዊ ዴሞክራሲ' ፍሬነገር እንኳንስ የኢትዮጵያ ምልአተ ሕዝብ፣ በኢሕአዴግ ዙርያ ያሉትን ሊሂቃንና ካድሬዎች እንኳ የገባቸው አይመስለኝም። ለነገሩ ኢሕአዴግ 'አብዮታዊ ዴሞክራሲ' አለ እንጂ በሌላ አነጋገር 'ዴሞክራስያዊ ማእከልነት' ማለት ነው። የ'ዴሞክራስያዊ ማእከልነት'ን ጽንሰሓሳብ ያስቀደመው (እንድያውም የፈጠረው) ቭላድሚር ኢሊች ለኒን ነው። ዋና ትርጉሙ ደግሞ አንድ በሥልጣን ጠገግ የተዋቀረ ፓርቲ ሆኖ፡ ሕብረሰተሰቡን በብቸኛነት የሚያስተዳድር ማለት ነው። የለኒኑ 'ዴሞክራስያዊ ማእከልነት' እንደ ማንኛውም አምባገነናዊ ሥርዓት የፈላጭ ቆራጭ ፓርቲ የነገሰበት ስለሆነ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓትን አይፈቅድም። ሰለሆነም የልዩ ልዩ ፓርቲዎች ፍኩክር ወይም ውድድር አይኖርም። ሕብረተሰቡ በአንድ ኮሚኒስት ፓርቲ ብቻ ነው የሚተዳደረው። ነገር ግን በፓርቲው ውስጥ ነጻ የፖለቲካ ውይይት ይፈቀዳል፣ ነጻ ምርጫ አለ። እያንዳንዱ የፓርቲው አካል እንደየደረጃው በቀጥታ ከበላዩ ያለውን አካል ይመርጣል፣ ውሳኔዎቹም በዛው መጠን ይተላለፋሉ። በዚህ ዓይነት መዋቅር ደግሞ ፓርቲው ሌሎች ድርጅቶችና ማሕበራዊ ክፍላተ-አካላት፣ ከቤተሰብ እስከ ትምህርት ቤት እስከ ፋብሪካ መቆጣጠር ይችላል። አሁን በኢትዮጵያ የተከሰተው አዲስ ፖለቲካ፡ በተለይም ከ2002 ምርጫ በኋላ፡ ይኸው ነው። ግን በለኒኑ 'ዴሞክራስያዊ ማእከልነትና' በኢሕአዴግ 'አብዮታዊ ዴሞክራሲ' አንድ ልዩነት ቢኖር የለኒኑ የለየለት ኮሚኒስት ፓርቲ ሆኖ ኢሕአዴግ ግን አይደለም። ኢሕአዴግ የነጻ ገበያ ምጣኔሃብታዊ ሥርዓት ያስተናግዳል ግን የምዕራቡ ሊበራል ዴሞክራሲ ስለማይቀበል ድርጅቱ ከመሃል የተንጠለጠለ ገገር ፓርቲ ነው ማለት ይቻላል። ኢሕአዴግ ሁላችን በሚገባን በቀላል አማርኛ ምንነቱ ካልገለጸ በስተቀረ አብዛኞቻችን የ ጐማ እግሩ እጣ ይደርስብናል የሚል ስጋት አለኝ።

'ጥቍር አማሮች' (ምዕራፍ 6) ከርእሱ ጀምሮ የተምታታ ስለሆነ አንባብያን እንደ ገባቸውና እንደ መሰላቸው እንዲተረጉሙት ትቼዋለሁ።

'የጀግና አገር ዲምቢጥ' (ምዕራፍ 7) እንደ 'የቁሊቢ ሌሊት' እና በ 'ጋዜጠኛው ማስታወሻ' የተጠቀሱትን የደራሲው ሴት ጓደኞች የሚተርክ ነው። እውነቱን ለመናገር፡ ደራሲው እንደ ብዙ ሐበሻ ወንድ ሴት አሳዳጅ እንደነበረ ጥርጣሬ የለውም። በምዕራፉ መጀመርያ ገጽ ደራሲው እንዲህ ይላል፦ "በ1988 የጥምቀት በአል ምሽት በአጋጣሚ የተዋወቅሁዋት አንዲት ልጅ ልቤ ውስጥ ለዘልአለሙ ተሰንቅራ ቀርታለች። በመሆኑም የዚያችን ውብ ጮርቃ ታሪክ በዚህ መድበል ለማካተት ተገድጄያለሁ። አንዳንድ ጊዜ ትዝታን የሚመስል ፀፀት ከአእምሮ ሳይጠፋ ለረጅም ጊዜ ይቆያል። ርግጥ ነው፣ 'የፈሰሰ ወተት አይታፈስም' የሚሉት አይነት ነው። ህሊናዬ ውስጥ የቀረው ቍራጭ ፀፀት ግን በከባድ ጎርፍ እንኳ አይጠረግም።" (ገጽ 139)። አንድ የወደድኩት የደራሲው ባህርይ ቢኖር ደግሞ ስሜቱንና አመለካከቱን በግልጽ፡ ፍርጥር አድርጎ ስለሚያቀርብ ነው። ስሜቱን በግልጽ የሚናገር ሰው በርካታ ጠላቶች ሊያፈራ ይችላል (በተለይ በገዛ ራሳቸው የማይተማመኑና ንቃተ ኅሊናቸው ያዘቀጠ ከሆነ) ፣ ብዙ ሰዎች ግን ያከብሩታል።

'ጀቤ ልክ ነበር' (ምዕራፍ 8) ስለ ጀ/ል አበባ ተክለሃይማኖት (ጀቤ) ቢሆንም ቅሉ እንደ ርእሱ ግን እምብዛም ስለ ጀነራሉ አይናገርም። የምዕራፉ ቍምነገርና

መልእክት የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት ስለሚያገኟቸው የስርቆት የማስተርስ የትምህርት ማዕርጎች እና 'የሐሰት ዶክትሬት' ለማጋለጥ መመከሩ ነው። ለዚሁ እውነታ ግን ደራሲው አንድ ተጫማሪ ሐቅ ማከል ነበረበት፣ የነዚህ የሃሰት ወይም ፎርጅድ ዲግሪዎች ምንጭ በአውሮጳ ሆኖ በተለይም Open University ከተባለው የእንግሊዝ ዩኒቨርሲቲ እና አምስተርዳም ዙርያ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ናቸው። ከዚሁ የተያያዘ መቅረብ ያለበት ሐተታ ደግሞ አውሮጳውያን ጥቁር ሕዝብን ስለሚንቁ በፖለቲካ አመራር ለሚገኙ ግለሰቦች የግልባጭ (ካርቦን ኮፒ) ዲፕሎማ ይሰጡና የሦስተኛ ዓለም ሕዝቦች አዘቅት ውስጥ እንዲነከሩ ያደርጋሉ።

'የወያኔ ሚስጢሮች' (ምዕራፍ 9) አስመልክቶ "አንድ ሙሉ መጽሐፍ በጻፍኩ ነበር" ይላል ደራሲው። እውነቱ ሊሆን ይችላል፣ ያጋነነም አልመሰለኝም። ነገር ግን ደራሲው ይኽን ሁሉ ሚስጢር ማወቅ የቻለው የኢሕአዴግን የስለላ አውታሮችን በቀላሉ መድረስ ስለቻለ ነው ወይስ 'ካበለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው' የሚያሰኝ ነው? ምናልባት በዚህ በኩል አንባብያን እውቀት መገብየትና ሚዛናዊ መረጃ ማግኘት የሚችሉት በኢሕአዴግ በኩል የመከላከያ ምላሽ ሲሰጥ ብቻ ነው።

'ፃድቃንና ፆሮና' (ምዕራፍ 14) በኢትዮጵያና-ኤርትራ ጦርነት ጊዜ በፆሮና አካባቢ የተፈጠረው ውዝግብን ነው የሚተነትነው። በፆሮና በኢትዮጵያ የመከላከያ ኃይሎች የደረሰው ጉዳት፣ የወታደራዊ ታክቲክና ስትራተጂ በስውር ስለፈረሰና ሻዕብያም መረጃ ቀደም ብሎ ስላገኘ ነው የሚል በሰፊው ተወርቶ ነበር። ደራሲው በዚህ ረገድ አዲስ ነገር አላመጣም። ነገር ግን ምዕራፉ ሌላ መላምትና ፍሬ ነገር ሊጠቁም ይችላል። የፆሮና ጉዳት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ-ኤርትራ ጦርነት ከግጭቱ ባሻገር ቲያትርም ታክሎበት ሊሆን ይችላል። የጦርነቱ መንስኤ ባድመ ወይም የድንበር ጥያቄ ሳይሆን ኢኮኖሚ በተለይም የገንዘብ ልውውጥ ነው። ይኽ ችግርም በቀላሉ መፈታት የሚችል ነበር፣ እንድያውም አንዲት ጥይት ሳትተኮስ በሰላም መፍታት ይቻል ነበር። ዳሩ ግን የማናውቀው ብልሃትና ጉድ ሊኖር ስለሚችል ያልታደለው የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝብ ከመናቆር አልፎ ወደ ግዙፍ ጦርነት ገባና 90ሺ ሰው ደመ-ከንቱ ሆኖ ቀርቷል።

'ያልተጻፈ መጽሐፍ' (ምዕራፍ 15) የተሰኘውን ምዕራፍ ሳነበው የኢትዮጵያ የየካቲት አብዮት ከመደንፋቱ በፊት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያኔ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ) አካባቢ የነበሩትን የፖለቲካ ተዋንያን ወይም የተማሪ ንቅናቄ መሪዎች ስሞች ስለሚጠቅስና ስለወሎም ስለሚያወራ አንድ ከወሎ የሆነ ወዳጄ ጋር ደወልኩና በከፊል አነበብኩለት፣ ምዕራፉም እውነትነት እንዳለው ሁለታችን ተስማምተናል። ነገር ግን የዚሁ ምዕራፍ ሰነድ ባለቤት በሂወት ስለሌለ የሚቹ ልጅ ነው ለደራሲው መረጃውን የላከለት፣ ስሙ ግን እንዳይከሰት አደራ ስላለ ተስፋዬ ገብረአብ አደራነቱን አክብሯል። ያልገባኝ ነገር ግን ይኽ ያልተጻፈ መጽሐፍ የሚባለው ሰነድ ምንም ሚሰጢርነት ስለሌለው ለምንድነው የሚቹ ልጅ ከቅጡ ያለፈ ጥንቃቄና ፍርሃት የተጠናወተው? ወይስ ደራሲው ጸሐፊ ስለሆነ ሳይታወቀው (በውስጠታዋቂነት) ቅመም ጨማምሮበታል?

'ዘርና ዘርማንዘር' (ምዕራፍ 20) ከሁሉም ምዕራፋት በይበልጥ ወድጄዋለሁ። ይኸውም በሁለት ምክንያት ነው፦ 1) በ'ጥቍር አማሮች' (ምዕራፍ 6) የተሰነዘሩትን

አስፈላጊ ያልሆኑትን የጎጥ አመለካከትና የብሔር ማንነት ምዕራፍ 20 ያስተካክለዋል፣ 2) ምዕራፉ የኔን አመለካከት ከሞላ ጎደል ያንጸባርቃል።

ባሁኑ ጊዜ "ጐሳና ጐሰኛነት የአካባቢያችን አጀንዳ ሆነዋል" ብሎ የጠቀሰውን ትክክል ሆኖ ዋናው ፍሬ ነገሩ ግን "የላቀው ራእይ በአፍሪቃ ቀንድ ደረጃ ማሰብ ነው" ያለውን ነው። እኔ ለነገሩ በአፍሪቃ ቀንድ አጀንዳ ብቻ አልረካም፣ የማራምደው የጠቅላላ አፍሪቃ አጀንዳ ነው። ነገር ግን አሁን በተጠናወተን የጎጥ በሽታ የአፍሪቃ ቀንድ አመለካከት እጅግ የላቀና የምንመኘው ጉዳይ ይሆናል። ለማንኛውም ደራሲው ምናልባት ሳያገኛቸው ቀርቶ ያለነበባቸው የኔ ጽሑፎች እንድያነብ እጋብዘዋለሁ። የሚከተሉትን ሁለት ርእሰ-ነገሮች በአፍሪቃ ልማትና ትምህርት ተቋም ወብሳይት ([www.africanidea.org](http://www.africanidea.org)) ይገኛሉ፡ 1) 'ለኢትዮጵያ የሚበጅ ስትራተጂ መቀየስ የሁላችን ኃላፊነት ነው' ፣ 2) ማን ነው ኢትዮጵያዊ?

'ቦረና! የስልጣኔ ዋሻ' (ምዕራፍ 23) ቍም ነገር ያዘለች ምዕራፍ ነች፣ ስለ ኦሮሞ የገዳ ሥልጣኔ እና የሥነ ከዋክብት ጥናትና ምርምር ታወራለች፡ መልካም ነው፣ ምክንያቱም የኦሮሞ ሕዝብ ታሪክ በማንቋሸሽ የጻፉ ተማራማሪዎች ስለነበሩ ሐቁን ታሪክ ይገለጣል፡ ይስተካከላል። ከዚሁም በተያያዘ ደራሲው አንጋፋውን ምሁር አስመሮም ለገሰን ምስጋናና ከበሬታ መስጠቱ ተገቢ ነው። ነገር ግን የሥነ ከዋክብት ጥናትና ምርምር ጠቅላላ አፍሪቃ፡ ሜሶፖታምያ (አሁን ኢራቅ)፡ ህንድና የጥንት ማያና አዝተክ ሥልጣኔዎች (አሁን መክሲኮ) ያካተተ ነበር። ጥንታውያን ግብጾችና ኢትዮጵያውያን እጅግ በረቀቀ መልኩ ስለ ከዋክብት እውቀት ነበራቸው። የሁለቱም አውደ አዋርህ (የግብጽ ከጠፉ ቀይቷል፡ የኢትዮጵያ ግን አሁንምን አለ) መሰረት የሆነውም የከዋክብት ምርምር፣ የፀሐይና ጨረቃ እንቅስቃሴ፣ እንዲሁም የወቅቶች ልውውጥ ነው። ይኸንን ታሪክ በሚመለከት በሰፊው ማወቅ ከተፈለገ ኢቫን ቫን ሰርቲማ የጻፈው መጽሓፍ (Blacks in Science) አለና ቢነበብ መልካም ነው።

All Rights Reserved. Copyright © IDEA, Inc. አልትተ ገላውዴዎስ ኣርኣያ

## ነጻነትና እና ዳኝነት በኢትዮጵያ ስየ አብርሃ ሲግነቸር 2002

'ነጻነትና ዳኝነት በኢትዮጵያ' በስየ አብርሃ 'የሰባት ዓመት ሰቆቃ' የተመሰረተ የራስ-ህይወት ትረካ ሆኖ በመግብያው እንደተገለጸውም ደራሲው የደረሰበትን የፖለቲካ ውጥረትን ነው የሚተነትነው፦ "በመጋቢት ወር 1993 ዓ.ም. ላይ የህወሐት ማእካላዊ ኮሚቴ ለሁለት መሰንጠቁን፣ ጠ/ሚኒስትርና የህወሓት ሊቀመንበር በነበረው በአቶ መለስ ዜናዊ የተመራው ቡድን እኔ የነበርኩበትን ቡድን በጉልበት ከፓርቲና ከመንግሥት ገፍትሮ ማስወጣቱን ተከትሎ እኔን ከሰባት የቤተሰቤ አባላት ጋር አስሮኛል። የታሰርን ዕለት ማታውኑ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽ/ቤት የወጣው መግለጫ አሳሪያችን የፖለቲካ ባለጋራዬ ራሱ የህወሐት ሊቀመንበር አቶ መለስ ዜናዊ መሆኑን፣ በእስሩ ላይ ዳኛም ይሁን የፀረ-ሙስና ኮሚሽን እጁን አለማስገባቱን ከራሱ ከመግለጫው ይዘት ግልፅ ሆኗል።"

መጽሐፉ ብዙ ዓበይት ነገሮችንና ከኢትዮጵያ ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታ የሚዛመዱ ነጥቦችንን በዝርዝር ስለሚያቀርብ ሁሉንም በዚህ አቃቂር መወያየት ስለማይቻል የላቁና አንገብጋቢ ብዬ የገመትኳቸውን ፍሬ ነገሮችን ብቻ አቀርባቸዋለሁ።

በገጽ 29 ስየ 'ብርሌ ከነቃ አይሆንም ዕቃ' የሚለውን በ1993 በህወሐት ውስጥ የተከሰተውን የመሰረተ-ሐሳብ ልዩነቶች (የኤርትራና ኢትዮጵያ ጦርነትና የአልጀርስን ሰምምነት ብሎም ያስከተለው ውዝግብ) አስመልክቶ እንዴት ፓርቲውን ለሁለት እንደሰነጠቀው ለማሳያት ነው። የህዋሐት በሁለት መገመስና የመለስ ቡድን በአቸናፊነት መውጣት የነስየም መቸነፍ ብቻ ሳይሆን ከፓርቲው መባረር ያደባባይ ሚስጢር ሆኖ ዓለም በጠቅላላ ያወቀው ጉዳይ ነው።

ሌላ ብዙ ሰው ያልገባው ግን እንዴት ብለው ነው እነ መለስ ባቸናፊነት የወጡት፣ እነ ስየ ግን እስከ መባረር የደረሱት የሚለውን ነው። ይህ የፖለቲካል ሳይንስ ትንተና ያስፈልገዋል፣ ተመልሼ እስከምመጣበት ድረስ ግን አንዳንድ እውነታ ስየ ከጻፋቸው መጀመርያ ልጠቃቅስ፡-

"በሕወሐት ማእከላዊ ኮሚቴ የተፈጠረው የሐሳብ ልዩነት ለወራት ስብሰባ ተቀምጦም የሚፈታ አልሆነም። መጨረሻ ሃሳብን በሃሳብ ማሸነፍ መሆኑ ቀረ እና ድምጽን በማስፈራራት እና በልመና የመግዛቱን ዘመቻ አቶ መለስና አቶ ስብሐት ተያያዙት።" (ገጽ 35)

"አቶ መለስ አቶ ገብሩ አስራትን ከትግራይ ብሔራዊ መንግሥት ፕሬዚደንትትነት ለማውረድ የተጠቀመበት መንገድ..." "የፓርቲውን ዴሞክራሲያዊ ማእከልነት መርህና አሠራር" በመጠቀም ነው፡ "አቶ ፀጋይ በርሄ እና አብረውት የክልል ባለሥጣናትና ካድሬዎች ከፓርቲው ሊቀመንበር በተሰጣቸው መመሪያ መሠረት ከክልሉ ሕገ-መንግሥት ውጭ በሆነ ሥርዓት አቶ ገብሩ ባልተገኙበት ሁኔታ የክልሉን ምክር ቤት ጠርተው አቶ ገብሩን 'ከሥልጣን ወርደሃል፣ በአቶ ፀጋይ በርሄም ተተክተሃል አሉት።" (ገጽ 48)

"መጋቢት 1993 ላይ ልዩነታችን ይፋ ከወጣና እኛ ተገፍተን ከወጣን በኋላ፡ መቐለ ላይ በተጠራው የካድሬዎች ስብሰባ ላይ በዚያው አከባቢ የነበሩት መኮንኖች ስብሰባውን እንዲቀላቀሉ በማድረግ፣ አቶ መለስ ሠራዊቱን ወደ ፖለቲካው ልዩነት በመጨመር ረገድ የመጀመርያውን ይፋዊ እርምጃ ወሰደ። ይህ እርምጃ ሕገ-መንግሥቱን የሚጥስና እና የሠራዊቱን የወደፊት እጣ ፈንታ የሚነካ ትልቅ እርምጃ ቢሆንም፣ አቶ መለስ ይህንን እርምጃ ሲወስድ በወቅቱ የጦር ኃይሎች ኤታ ማዦር ሹም የነበረውን ሌ/ጀነራል ፃድቃን ገብረትንሳኤ እንኳን አላማከረውም። በገዛ ፈቃዱ ነበር እንዲቀላቀሉ ያደረገው፡" (ገጽ 58)

አሁን ወደ ፖለቲካል ሳይንስ ትንተና ከሄድን መጀመርያ ማወቅ ያለብን ማንኛውም መንግሥት ሦስት ነገሮችን ማከታት ይኖርበታል፡- 1) ሕግና ድርጅታዊ መዋቅር፣ 2) ወሳኞች (ሊሂቃን) እና 3) የመስተዳድር ሹማምንት (bureaucrats) ። ሦስቱ ለማንኛውም የፖለቲካ ሂደት ወሳኝ ሚና ይኖራቸዋል። ሊሂቃኑ ሁለት ዓይነት ናቸው፡- ሀ) ውሁዳን፣ ለ) ብዙሃን። በውሁዳኑ የመወሰን ሥልጣን በትንሽ ሰዎች

እጅ ይወድቃል፣ ስለሆነም ሥርዓቱ አምባገነናዊ ይሆናል። በአንጻሩ በብዝሃኑ የፖለቲካ ሥልጣን ሰፋ ባለ መልኩ የወሳኝ አካላት ስለሚጋሩት አንድ ወይም የተወሰኑ ግለሰቦች ብቻ መንግሥትን መቆጣጠር አይችሉም። የብዝሃኑ ሥርዓት ዴሞክራስያዊ ስለሆነ ሕዝቡ በፖለቲካ መስክ ተሳትፎ ይኖረዋል፣ የሕግ የበላይነት አለ፣ ባለሥልጣናት በግልጽነት ከመስራታቸውም በላይ ለሕዝቡም ተጠያቂ ናቸው። እንዲህ ዓይነት ሥርዓት በውሁዳን የለም፣ ለዚህም ነው አምባገነናዊ ገዢዎች ሕዝቡን እንደፈለጉ የሚያዋክቡት። ይህ ትንተና ግን ከፍ ብለን የጠቀስናቸውን በፓለቲካ መድረክ ላይ የማቸነፍና የመቸነፍ ጉዳይ ሙሉ በሙሉ አይገልጸውም። ታድያ ዋናው ጥያቄ መሆን ያለበት ማእካላዊ መንግሥቱን ማን ይቆጣጠረዋል? ነው። ይኸንን ጥያቄ ከመለስን ደግሞ እነ ስየ ለምን ከሥልጣን እንደተባረሩ በቀላሉ ማወቅ እንችላለን። ኢህአዴግ ሥልጣን ከጨበጠ ጀምሮ ማእከላዊ መንግሥትን የተቆጣጠረው የነመለስ ቡድን ነው፣ ማእካለዊ መንግሥት ደግሞ ዋናው አስፈጻሚ አካል ሆኖ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚቆጣጠራቸው አውታሮች ያሉበት ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዋና ፈጻሚ፣ የሚንስተሮች ምክር ቤት ሊቀመንበር እና የጦር ኃይሎች ዋና አዛዥ ነው። የዓለም አቀፍ ግንኙነቶች በውጭ ጉዳይ ሚኒሰተር በኩል ይቆጣራል፣ ድኅንነት፡ ፖሊስ፡ ፋይናንስ በቊጥጥሩ ስር ናቸው። የመለስ ቡድን ይኸንን ሁሉ ይቆጣጠራል። በተቃራኒ የስየና የገብሩ ቡድን ከማእካለዊ መንግሥት ርቀው በዳርቻ የመንግሥት ክንፍ ነበር የተቀመጡት፣ ስለሆነም ሥልጣናቸው በጣም ተራና አነስተኛ ነበር። ስየ መጀመርያ የመከላከያ ሚንሰተር በነበረበት ጊዜ ለማእከላዊ መንግሥት ቅርበት ነበረው፣ ወደ ትግራይ ከተዛወረ በኋላ ግን ተራውን ሥልጣን ነበር የጨበጠው፣ ያውም የሽረት ዓይነቱ! ስለሆነም እነ መለስ የነስየን ቡድን ማባረሩና ማሰሩ በፖለቲካ ዓለምና ከፖለቲካል ሳይንስ ትንተና አንጻር ካየነው የሚያስደንቅ አይሆንም። ከዚህ ውጭ ሕገ-መንግሥቱን በመጣስ አሰሩ፡ አባረሩ፡ ገደሉ ወዘተ ቢባል የውሁዳን ባህርይ መዘንጋትና የዋህ የፖለቲካ እንስሳ መሆንን ነው የሚያሳየው።

ስየ የአሰራር አርአያነት ወይም ጥበብ በትንተናው አልተጠቀመም እንጂ ከላይ ያስቀመጥናቸውን የፖለቲካል ሳይንስ አገላለጽ በተዘዋዋሪ መንገድ ያስቀምጠዋል። ለምሳሌ በገጽ 50 “ፓርቲው የሁሉም አባላት መሆኑ ይቀርና የአቶ መለስ ወይም የአንድ የተወሰነ ቡድን ተደርጎ ይታያል” ያለውን የውሁዳን ሥርዓት ፖለቲካ ነው የሚያንጸባርቀው። በነገራችን ላይ ከፍ ብለን እንደጠቀስነው ገዢው ፓርቲ መንግሥቱን ስለሚቆጣጠር የመንግሥት ዘርፎች ሁሉ በፓርቲው አምሳል ነው የሚቀረጹት፣ ስለሆነም ከፓርቲው ፍላጎት ውጭ ተግባራቸውን ማከናውን አይችሉም። ለዚህም ነው ስየ ፍርድ ቤቶቹን አስመልክቶ በ ‘ትሻልን ትቼ ትብስን አገባሁ’ (ገጽ 53) በሚል ምሳሌ የገለጻቸው።

በገጽ 54 የአልጀርስ ውሳኔ በኢህአዴግ ወስጥ ልዩነቶች መፍጠሩ ይገልጽና በውዝግቡ ምክንያት ግን ህወሐት ተበተነ እንጂ ሌሎቹ የኢሕአዴግ ድርጅቶች ግን እንዳሉ ቀጥለዋል ይላል። ይህ የሚያሳየው ዋናው የኢሕአዴግ አካል ወያኔ ችግር ገጥሞት እያለም ለመቆጣጠር መቻሉና ሌሎቹ ተሳቢ ድርጅቶች ግን በዚሁ ረገድ አስተዋጽኦ እንዳልነበራቸው ነው። በተጨማሪ በውሁዳኑ ሥርዓት ምንም እንኳ በገዢው ፓርቲ ያሉት ባለሥልጣናት መንግሥቱን ቢቆጣጠሩ በእንዲህ ዓይነት

አምባገነናዊ ሥርዓት የውስጠ-ኃይል አመራር (core) ስላሉ የበላይ ውሻና የበታች ውሻ መኖራቸው አይቀርም።

የዚሁ የበላይና የበታች የሥልጣን ሽኩቻና ውስብስብ ያሉ የፖለቲካ ግንኙነቶች እንደ አብነት ማስቀመጥ የምንችለው ስየ አብርሃ በገጽ 57 ያቀረበልንን ሐተታ ነው። እንዲህም ይላል፦

“የአቶ መለስ ነገር እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል ካለችው እንስሳ የማይሻል ፈሊጥ ሆነና በጦርነት መሃል እያለን ክረምቱን ሙሉ ስራ አስፈጻሚውን እኔ ያልኩትን ካልተቀበለ ብሎ በስብሰባ አስሮት ከረመ። ሙግቱን እሰኪጨርስ ድረስ ተከራክሮ ስራ አስፈጻሚውን ማሳመን ሲያቅተው ደግሞ ምክር ቤቱ ይጠራልኝ እሱን አሳምኜም ውሳኔአችሁን አስገለብጣለሁ አለን። እኛም የበላይ በሆነው የድርጅቱ አካል የመደመጥ መብቱን አክብረን በዚሁ እየተንቀሳቀስን እያለን ደግሞ እንደገና ጀነራሎችን ወደ ፓርቲ ፖለቲካ ካልመለስኩ ሲለን ‘ይኸማ ሊሆን አይችልም’ ብለን ማቆም ነበረብን።”

በእርግጥ እነ ስየ መለስን በብዙ ረገድ ሥልጣኑን ለመቆጣጠር ሞክረዋል ግን ቅድም እንደተገለጸው እነሱ ተራ ሥልጣን ስለነበራቸው ከመንፈራገጥ ማለፍ አልቻሉም። አንዳንዴም የመለስ ቡድን ከአንዳንድ ባለሥልጣናት የግጥምያ ጥሪ አጋጥሟቸው ነበር። ለምሳሌ ብ/ጀነራል ታደሰ በርሀ (በመከላከያ ሚኒስተር ጠቅላይ መምርያ ውስጥ የአስተዳደርና የሲቪክ መምርያ ሃላፊ የነበረው) መለስ ላዘዘውና ለፈለገው ምላሽ ሲሰጥ “እኔ ከህወሐት ተሰናብቼ ይህንን መለዮ እና ማዕረግ የለበስኩት ለኢፌድሪ ሕገ-መንግሥት ለማገልገል እንጂ የአንተን የቡድን ፖለቲካ ለማራማድ አይደለም፣ ስለሆነም እንኳንስ ይህንን ላስፈጽምልህ ይቅርና ከእንግዲህም አንተ በምትመራው መንግሥት ስር ለመስራት ስለማልፈልግ አሰናብተኝ” (ገጽ 59) በማለት በድፍረት ግጥሚያውን ተያያዘው። ብ/ጀ/ል ታደሰ ‘ይኸንን ላስፈጽምልህ ይቅርና’ ያለውን መለስ በሕወሓት በ1993 ለተፈጠረው ውዝግብ ለማርገብ መቐለ ውስጥ በተደረገው የድርጅቱ ማእከላይ ኮሚቴ ስብሰባ ጀነራሎቹም እንዲሳተፉ በመፈለጉ ነበር። የሆኖ ሆኖ ግን ምንም እንኳ የብ/ጀ/ል ታደሰ ቆራጥነትና ጽኑ እምነት የሚደነቅ ቢሆንም በውሁዳን ፖለቲካ ግን ውጤቱ አሉታዊ ሊሆን ይችላል፣ በተለይም የኛ የእልህና ቂም በቀል ፖለቲካ ታክሎበት፣ እንኳንስ ዘንቦብሽ እንድያውም ጤዛ ነሽ ነው የሚሆነው።

ደራሲው በገጽ 60 እንዳመለከተውም አቶ መለስ “በሠራዊቱ ውስጥ በተከታታይ በካሄደው ከፍተኛ ምንጠራ በርካታ መኮንኖች ከያሉበት ተለቅመው እንዲታሰሩ አደረገ፣ ጀነራል ጻድቃን እና ጀነራል አበበ ተክለሃይማኖትም ከነበሩበት ሃላፊነት ተነስታችኋል ተባሉ።” “የዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ እና አባተ ኪሾ ሥልጣን መልቀቅ፣ የአቶ አባተ ኪሾ መታሰር…” (ገጽ 71) ደግሞ ከላይኛው እርምጃ ጋር የተያያዘ ነው። ይህ የውሁዳን ሥርዓት ዓይነተኛ ምሳሌ ነው፣ መለስ እንደሆነ በህወሐትና ኢህአዴግ ውስጥ የራሱና የቡድኑ የተደራጀ ኃይል ስለፈጠረና መንግሥቱን ለመቆጣጠር ስለበቃ ነው የፈለገውን ማድረግ የቻለው። በዚሁ አኳያ ስየ በሐሳብ ደረጃ “ኢትዮጵያ ከፓርቲዎች የፖለቲካ ሽኩቻ ገለልተኛ ሆኖ ራሱን ችሎ የቆመ

የመከላከያ ተቋም ያስፈልጋታል” ያለውን በብዙሃንና ዴሞክራስያዊ ሥርዓቶች ብቻ ነው የሚሰራው። አለዛ ላም ባልወለበት ኩበት ለቀማ ነው የሚሆነው።

ከፍላጎት የመነጩ ስሜታዊ ገለጻዎች ባሻገር ግን ስየ በገጽ 60 “አፋኝ አገዛዞች ባሉበት አገር የነፃነት መንገድ የተዘጋ መንገድ ነው” ያለውን ትክክለኛ አባባል ነው። ነገር ግን ደራሲው በገጽ 70 “እንደ ሕገ-መንግሥቱ እንሂድ ከተባለ...” የሚለውን ሐረግ ከላይኛው አባባል ጋር የሚቃረን ነው። አፋኝ ቡድን ባለበት’ማ ሕገ-መንግሥቱ እንደማይሰራ የታወቀ ነው። እንድያውም ሕገ-መንግሥቱ የወረቀት ነብር ነው የሚሆነው።

በገጽ 74 እና 75 የተጠቀስቱን ‘አዋጆችና አንቀጾች’ ደግሞ እንደ ሕገ-መንግሥቱ የማይሰሩ ወረቀቶች ናቸው፣ ለዚህም ነው ስየ “ሕገ-መንግሥቱ በእስር የተያዙ ሰዎች ያለመናገር መብት አላቸው” ብሎ የጠቀሰውን ትርጉመ-ቢስ የሚሆነው። ‘ያለ መናገር መብት’ እንደ አመሪካ የመሳሰሉት የሕግ የበላይነት ያሉባቸው አገሮችና የዴሞክራሲ ስርዓት በበለጸጉባቸው ሕብረተሰቦች እንጂ እንደኛ ዓይነቱ የዴሞክራሲ ባህል ደብዛው በጠፋበት አይሰራም።

አስካሁን ድረስ አንባብያን ይማሩበት ዘንድ ከሚል አንጻር ስየን በፍርድ ቤቶችና በእስር ቤት የገጠመው ችግር አላነሳሁም። አሁን በመጠኑም ቢሆን እንደሚከተለው አግባብነት ባለው መልክ አቅርብያቸዋለሁ።

በገጽ 84 ስየ እስር ቤት ውስጥ “ለብቻ ከመሆን ሰው ማግኘት በጎ ነው” ያለውን መሰረታዊ የሰውን ባህርይ የሚያንጸባርቅ ነው። በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ ማንኛውም ሰውና እንስሳ ጓደኛነትን ማበጀት ይፈልጋል፣ ለጤንነታቸው ደግሞ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። ከሕበረተሰቡ የተነጠለ ሰው የኋላ ኃላ ይቀውሳል፣ ለዚህም ነው በእስር ቤት ለብዙ ዓመታት የቆዩ ሰዎች፡ በተለይም የቊም ወይም የጽኑ እስራት የተፈረደባቸው፡ ከተፈቱ በኋላ የአእምሮ መመሰቃቀል በሽታ የሚያጠቃቸው።

እንደገና በገጽ 84 ስየ “በብርድ የሚቀሰቀስ ከፍተኛ የአለርጂ ችግር ነበረብኝ” ያለውን እውነቱን ነው፣ ምክንያቱም በኤፕሪል 18 2010 በዋሽነግቶን ዲሲ በተደረገው የመጀመርያው የመድረክ ስብሰባ አዳራሽ ውስጥ በመጀመርያው ወንበሮች ረድፍ ተቀምጬ ስለነበር ስየ ከበስተጀርባው ከተቀመጠበት ወንበር ተንጠልጥሎ የነበረውን ወፍራም ጃኬት ጎትቶ ሲለብሰው አይቼዋለሁ። ያኔ በኤፕሪል (ሙቀት በጀመረበት ጊዜ) እንዴት ጃኬት ይለብሳል ብየ አሰላስል ነበር፣ አሁን ግን ነገሩ ገብቶኛል።

በገጽ 93 የተጠቀሱትን ‘ማሻሻያ አዋጆች’ ምን ያህል የአዋጅ መንግሥት ሥልጣኑን እንደጨበጠ ነው የሚያሳየን። የማይሰራውን ሕገ-መንግሥት ሳይቀር በአዋጅ ማጠፍ ይፈልጋል፡ ያኮላሻል። ስለሆነም ኢሕአዴግ ሕግ-አውጪ፡ ከሳሽ፡ አሳሪ እና ዳኛ ለመሆኑ የሚያስደንቅ አይሆንም። ስየም በተደጋጋሚ ይኸንን ሀቅ ነው በመጽሐፉ መግለጽ የሞከረው።

በገጽ 122 ስየ በእርሱ ላይ የተሰነዘረው የሙስና ክስ በግልጽ ይተነትነዋል። ብዙ ኢትዮጵያውያን የስየን ጀግንነት እንኳ ባይጠራጠሩት እንደ ማንኛውም የመንግሥት ባለሥልጣን፥ በተለይም የትእምት ወይም EFFORT ሃላፊ ሆኖ በሰራበት ጊዜ ግን በመጠኑም ቢሆን ሙስና ነካክቶት ሊሆን ይችላል የሚሉ አሉ። ደራሲው በመጽሐፉ እንደገለጸው ከሆነ ግን በተቃራኒ ከመጀመርያውኑ ራሱ ሙሰናን ይዋጋ እንደነበር ነው። እንዲህም ይላል፦ "በሙስና ላይ ያለኝ አቋም ግልጽ እና የማያወላዳ መሆኑንና ሙስና አለ ከተባለ ይጣራ ብለው የውሳኔ ሃሳብ ካቀረቡት የህወሐት ማእከላዊ ኮሚቴ አባላት አንዱ መሆኔን፣ ሆኖም ግን በአቶ መለስ የሚመራው ቡድን በዚህ ሃሳብ ከመደናገጡ ባሻገር ሃሳቡን ውድቅ በማድረጉ ነገሩ ራስሽ ታመጪው ራስሽ ታሮጪው ሆኖ እንዳረፈው የሚገልጽ ነው።"

በነገራችን ላይ የክሱ ምስረታ ሙስና ይሁን አይሁን ለስየ መታሰር አግባብነት አይኖረውም። ሰውየው የፖለቲካ እስረኛ እንደነበረ ከሳሽ መስራቹና ምልአተ ሕዝቡ ያውቃል። ስለሆነም ስየ ራሱን ለመከላከል በፍርድ ቤቱ ውስጥ ለዳኞቹ የሰጠው መግለጫ የፖለቲካ መግለጫ ነው ብለው ሐሳቡን ተቀባይነት እንደሌለው ነግረውታል። ነገር ግን ዐቃቤ ሕግ መንበረ ፀሐይ የስየን ጠበቆች ሲያስፈራራና ፍርድ ቤቱ ብይን ሲሰጥ ፖለቲካዊ መሆኑን ዘንግተውታል።

ከገጽ 150 እስከ ገጽ 182 ዐቃቤ ህግ ያቀረባቸው አስር ምስክሮች፥ ስየ በበኩሉ ለምስክርነት የጠራቸው የድሮ ጓዶቹና ባልደረቦቹ እንዲሁም ሌሎች የድሮ ባለሥልጣናት፣ እንዲሁም የተሰጠው ብይን በዝርዝር ቀርበዋል። በዐቃቤ ሕጉ ከተጠሩት ሰዎች አንዷ ወ/ሮ አብርሀት ሃብተማርያም (የጽሕፈት መኪና ስህተት ይሁን 'አብረኸት'ም ተብላለች) ስየ ትእምት ኃላፊ በነበረበት ጊዜ ዋና ጸሐፊ የነበረች ነች። ወ/ሮ አብረሀት ዐቃቤ ህጉ የሚፈልገውን ስላልመለሰችና እውነቱን ስለተናገረች ብቻ "አቶ ስብሃት ነጋ ሂጂ ስየ ይቅጠርሽ ብሎ ከነበረችበት ሥራ እንድትባረር አደረገ። በዚህ ምክንያትም ችግር ላይ ወድቃ ሥራ እስከምታገኝ ድረስ ከ3 ዓመት ባላይ ተንከራታለች።" (ገጽ 151)

ከዚሁ በዓቃቤ ሕጉ የሚቀርቡ ምስክሮች አንዱ ታምራት ላይኔ ሆኖ ከነሱ ጋር ግብግብ እንደያዘና በእምነቱም እንደጸና የሚየሳይ ሐተታ ደግሞ በገጽ 156-57 ቀርቦልናል። ታምራት ላይኔ (በኢህአዴግ ዘመን የመጀመርያው ጠ/ሚንስተር) 'ሦስት ጊዜ እንደካደ (ኢሕአፓን፥ አገሩን፥ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን)' አድርገው የጻፉ ሰዎች ነበሩ። በሙስናም ተከሶ ነበር፣ ይኸንንም እርሱ ራሱ ከመለስ ዜናዊ ጎን ለጎን ቆሞ በኢትዮጵያ ተለቪዥን ሕዝቡ እያየው ያመነበት ጉዳይ ነው። ስየ በጻፈው ግን ታምራት ሌላ የማናውቀው በጎ ገጽ ሊኖረው ስለሚችል የሚከተለውን ማንበቡ አይከፋም፦

"በኢህአዴግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውስጥ በአቶ ታምራት ጉዳይ ላይ የተወያዩትና የፖለቲካ ውሳኔ ያሳለፉት ሰዎች ተገልብጠው እኔ አቶ ታምራትን የበደልኩ ሰው አድርገው በማቅረብ 'ተበቀል' ብለው አቶ ታምራት ጋር ሲሉኩበት የአቶ ታምራት መልስ 'እኔ የበቀልተኞች መሳርያ አልሆንም' የሚል ሆነ።

'የጻፍከወን ወረቀት አግኝተናልና የጻፍኩት እነሱ ስላግባቡኝ ነው ብለህ በስየና በአሰፋ ላይ ለመመስከር ፈቃደኛ ካልሆንክ ይህን የሰነድ ማስረጃ ይዘን ባንተ ላይ ክስ እንመሰርትብሃለን' አሉት። ለአቶ ታምራት የቀረበለት አማራጭ ወይ እኔንና አሰፋን በሐሰት ወንጅሎ ራሱን ማዳን፣ ራስን ማዳን ሲባል ደግሞ 'የተፈረደብህ ቅጣት እንዲቀነስ እናደርገዋለን' በሚል የተገባለት ቃል ተጠቃሚ መሆን ማለት ነው፣ ወይም ደግሞ 'የበቀልተኞች መሳርያ አልሆንም' ብሎ በእምቢተኝነት ተጨማሪ ክስ ቀርቦበት በ18 ዓመቱ ላይ ተጨማሪ የእስር ጊዜ ሲፈረድበት መቀበል ነበር። ከሁለቱ አማራጮች አንዱን እንዲመርጥ በተደጋጋሚ በመርማሪ ፖሊሶች ማግባብያ ቀርቦለት 'አልቀበልም፣ ብትፈልጉ ክሰሱኝ' አላቸው። በመጨረሻ ያኔ የፀረ ሙስና ኮሚሽን ዓቃቤ ሕግ የነበሩት አቶ ዮሃንስ ወ/ገብሪኤል ራሳቸው ከርቸሌ ድረስ ሂደው አቶ ታምራትን አነጋገሩት። 'እንግድያውስ በእነስየ ላይ አልመሰክርም ካልክ ክስ ልንመሰረትብህ ነው፣ ማስረጃ ተገኝቶብሃል' አሉት። አይ እንግዲህ ብትፈልጉ ልትከሱኝ ትችላላችሁ፣ ይህን ወረቀት እንድፅፍ አቶ ስየና ኣቶ አሰፋ አግባብተውኛል ብዬ ግን አልመሰክርም' አላቸው። በዚህ ተለያይተው አቶ ታምራትን ጨምረው ክሱን መሰረቱ።"

ታምራት ላይኔ ብያንስ ብያንስ በዚሁ በነስየ ክስ ላይ ለሐቅ ቆሟል። በሐሰት የሚመስክሩ ግን አልጠፉም፣ የዚሁ ምሳሌ በደራሲው የቀረበው የአርከበ ዕቁባይ ምስክርነት ነው። "አቶ አርከበ ምስክርነት ሲሰጥ፣ ትራንስ ኢትዮጵያ ለገዛቸው መኪኖች 'ሻጭ ማን ነበር?' ሲባል 'አምቼ ኢቬኮ' ነበር ያለው። 'አምቼ ኢቬኮ የሚባል ድርጅት አለ ወይ' ብለው የእኛ ጠበቆች ሲጠይቁት። 'የለም' አለ። 'ታድያ የሌለ መሆኑን እያወቅክ ለምን አምቼ ኢቬኮ ትላለህ? ሻጩ ማን ነው?' ተባለ እንደገና 'አምቼ' አለ። አንደኛው የአቶ አርከበ የሀሰት ምስክርነት ይህ ነበር።"

የአቃቤ ሕግ ክስ መስራችነት፣ የሐሰት ምስክርነት፣ የሐቅ ምስክርነት፣ የጠበቆች ሙጉት፣ የዳኞች ፍርድ ወይም ብይን መጨረሻው የልበ ወለድ ድራማ ነው የሚሆነው። ሐቀኛ ብይን ሊገኝ የሚቻለው ዴሞክራሲ በሰፈነበትና የመንግሥት ባለሥልጣናት ለሕጉ ተገዢ ሲሆኑ ብቻ ነው። ስየ አብርሃ ፍርዱን ከተነገረው በኋላ ኢትዮጵያ ባሁኑ ጊዜ ፍትሐ-አልባ መሆኑዋን ለማሳየት መኩሯል፣ እንዲህም ይላል፦ "በዚህ ችሎት ፍትህ የማግኘት እምነቴና ተስፋዬ ከተመናመነ ቆይተዋል እና ብይናችሁ አላስገረመኝም፡ ነፃ የዳኝነት ስርዓት በሌለበት፣ ነፃ ፓርላማ በሌለበት፣ ብቸኛው ስልጣን መለስ በሆነበት አገር ፍትህ ይገኛል ብዬ አልጠብቅም።" (ገጽ 175)

ከገጽ 184 ጀምሮ እስከ ገጽ 241 መጽሐፉ በርካታ ቊም-ነገር አዘል ነጥቦችን ስለሚያቀርብ አንባብያን በይበልጥ የመጽሐፉን ይዘትና መልእክት ያላምጡ ዘንድ አጠር መጠን ባለ መልኩ ከዚህ በታች ትንተናዎች ቀርበዋል።

በገጽ 184 ደራሲው "ኢኮኖምያዊ እድገት ለማምጣት…ገንዘብ ለማግኘት የምዕራቡ ዓለም ድጋፍና ይሁንታ ያስፈልገዋል። …ምዕራባውያን ዋና ትኩረታቸው ዴሞክራሲን በማስፈን ላይ ብቻ የተወሰነ ባይሆንም የዴሞክራሲ ዕሴቶችን የሚያስተናግድ ምኅዳር እንዲፈጠር ይጠይቃሉ። በተለይ ደግሞ ዓይን ያወጣ አፈና በሚኖርበት ጊዜ ከገዛ ሕዝባቸውም ጥያቄ ስለሚያስነሳባቸው አፈናው እዲለዝብ

ይፈልጋሉ” ይላል። በመቀጠልም አቶ ስየ “ስለሆነም አቶ መለስ በአንድ በኩል “የኛ ሰው ነው” በማለት ሲቀበሉት፣ እርዳታ ሲሰጡትና ሲያቅፉት፣ በሌላ በኩል ደግሞ በአገራቸው ህዝብ በኩል የሚመጣባቸውን ጫና በመፍራት አፈናውን እንዲለዝብና ክፍተት እንዲፈጠር መጫናቸው አልቀረም” በማለት ይደመድመዋል።

ደራሲው ያለውን እንዳለ ሆኖ የነዚህ እርዳታ ሰጪ ምዕራብ ሃገሮች የውጭ ፖሊሲና በታዳጊ ሃገሮች፣ በተይም በአፍሪቃ ሃገሮች፣ ላይ ያላቸውን አመለካከት ግን በትልቅ ጥያቄ ማስቀመጥ ያለብን ጉዳይ ነው። በመጀመርያ እነዚህ የምዕራብ አገሮች ማንኛውም የውጭ ግንኙነት ከጥቅማቸው አንጻር ብቻ ነው የሚያዩት። በዚህ ረገድ ግን እነሱን ብቻ መውቀስ አንችልም፣ እነ ቻይናም ቢሆኑም በማንኛውም ግንኙኘነት ጥቅማቸውን ነው የሚያስቀድሙት፣ የራሱን ጥቅም የማያስቀድም አገር ካለ ደግሞ ወይ በቅኝ ግዛት የሚተዳደር ነው ወይም ደግሞ ነጻ ሆኖ ግን መሪዎቹ ለኃያላን አገሮች በማጎብደድ የአገራቸውን ሉዓላዊነት ለድርድር አቅርበውታል ማለት ነው። በተጨማሪም የሰለጠኑ ምዕራባውያን ሃገሮች ‘እርዳታ ለማድረግ የዴሞክራሲ ጥያቄ እንደ ቅድመ ሁኔታ ያሰቀምጡታል’ እንላለን እንጂ አምባገነኖችን ነው ብዙውን ጊዜ የረዱትና ያቀፉት። በዚህ ላይ የጠራ የፖለቲካ አቋም እዲኖረን ያስፈልጋል፣ ይህ ማለት ግን ከምዕራባውያን ጋር መስራትና ግኑኝነት መፍጠር የለብንም ወደሚለው አጉል ርእዮተዓለም ማዘንበል አለብን ማለት አይደለም። ወደድንም ጠላንም ከነሱ ጋር ግንኙነት መፍጠር አለብን፣ ጥቅማችን ለማራመድ ከፈለግን ግን ብልሃትና ዘዴ፣ እንዲሁም የላቀና የረቀቀ የፖለቲካ ራእይ ይጠበቅብናል።

በገጽ 188 በ1997 የተካሄዱትን ቅድመ-ምርጫ ክርክሮች አስመልክቶ ደራሲው በዚህ መልክ ነው ያቀረበው፡ “ኢህአዴግ ትኩረቱን በተከፈቱት ት/ቤቶች ብዛት እና የትምህርት ዕድል ባገኙት ህፃናት ቁጥር ላይ ሲያተኩር ተቃዋሚዎች ደግሞ በፖሊሲውና በጥራቱ ላይ ነበር ያተኮሩት። በመሆኑም ኢህአዴግ በዚህ ላይ የተመኘውን ነጥብ አላስመዘገበም። ይህ ስለመሆኑ ደግሞ የኢህአዴጎቹ ተካራካሪዎች አቶ ተፈራና ወ/ሮ ገነት ዘውዴ ‘ለተሰራው ሥራ እንኳን እውቅና የማትሰጡ ናችሁ፣ በስርጭት በኩል የመጣውን ለውጥ እንኳን በጎ ለውጥ ነው ብላችሁ ለመቀበል አልቻላችሁም፡ ለምን የሠራነውን ሥራ አላመሰገናችሁም?’ የሚል ደካማ የክርክር አቅጣጫ እስከመያዝ ደርሰው ነበር።” የሚገርም ነገር ቢኖር ግን በ2002 ቅድመ-ምርጫ ክርክሮችም የኢህአዴግ ተወካዮች ከ97ቱ ጋር በይዘትም በቋንቋም አንድ ዓይነት የክርክር ነጥቦች መሰንዘራቸው ነው።

በገጽ 189-190 ደራሲው በ1997 ቅንጅት ያሳየውን ድክመቶች ገንቢ ነቀፌታ በሆነ መልኩ አስቀምጠታል፦ “ቅንጅቶች ለተፈጠረው ያልተጠበቁ የሁኔታዎች አካሄድ ዝግጁ አልነበሩም፣ ሁኔታው እየተለወጠ መሆኑ ምልክት ሲታይም ለዚሁ የሚመጥን ፕላን አልያዙም፣ በቅስቅሳውና በምርጫ ዘመቻው ነበር የተጠመዱት፣ ለዚሁ ባለቤት ላጣው ሥራም ኋላ ላይ ዋጋ ከፍለውበታል። ምርጫው ተካሂዶ ውጤቱ ሲታወቅ እህአዴግ ለሁኔታው ያዘጋጀውን መልስ ይዞ ብቅ አለ። የመጀመርያው መልስ የምርጫው ዕለት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የተነበበው የአስቸኳይ ጊዜ የሚመስለው አዋጅ ነበር። ቅንጅት የራሳቸው ስትራተጂ ስላልነበራቸው የቀራቸው መንገድ ለኢህአዴግ እርምጃ ዘገምተኛ መልስ መስጠት ብቻ ነበር። ቀደምትነቱን (the initiative) ለኢህአዴግ ለቀው እነሱ ተከታይ ሆኑ።”

ስየ በቅንጅት ያደረገውን ሂስ ከሞላ ጎደል እኔም ያኔ ‘ለመለስ ዜናዊ ያልተነፈገውን ለብርሃኑ ነጋ ይሰጠዋል’ በሚል ርእስ በጻፍኩት አቃቂር ውስጥ ሰንዝሬው ነበር። ሆኖም ግን በትግል ከተሰማራ ድርጅት ይልቅ ከውጭ ሆነው ለሚታዘቡ ሰዎች ነቀፌታ ማቅረብ ይቀልላቸዋል፣ ልክ እንደ ኳስ ግጥምያ ታዛቢዎቹ በተጫዋቾቹ ላይ ውርጅብኝ እና እርግማን እንደሚወረውሩ ማለት ነው። ይህ ያልኩበት ምክንያት በተቻለ መጠን የታገሉና የሞከሩ ድርጅቶች እንደ ቅንጅት ዓይነቶች በመጠኑም ቢሆን ፍትሕ እንድያገኙ ለማለት ነው። እውነቱን ለመናገር ግን ከኔ በላይ ስየ በትግሉ ዓለም ስለተሰማራ እንደ የኳስ ጨዋታ ቲፎዞ እንዳልሆነ ማሳሰብ አይፈልጋሉ። ከዚሁ ጋር አያይዘን ግን አሁንም ቢሆን (በምርጫ 2002) መድረክ ‘ያልተጠበቀ ሁኔታ’ አላጋጠመውም? አሁንም ኢሕአዴግ ‘ያዘጋጀውን መልስ ይዞ አልቀረበም’? እኛ ነን ያቸነፍነው፣ በ99.6 ከመቶ ስላቸነፍን ከ547 የፓርላማ ወንበሮች 545 አግኝተናል አላለም?

በገጽ 190 ኢትዮጵያ ምን ያህል ከዴሞክራስያዊ ሥርዓትና ፍትሕ እንደ ራቀች ደራሲው “ደርግ ከወደቀ ወዲህ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ የኢትዮጵያውያን ማደርያ እስር ቤት ሆነ፣ እስር ቤቶች ሞልተው የጦር ማሰልጠኛ ማእከላት ወደ አስር ቤትነት ተለወጡ” ይላል። ብዙ ጊዜ በታሪክ እንደታየው ሁሉ የሕዝብ ድጋፍ ያላቸውና በዛውም መጠን ሥልጣናቸው ሕጋዊነት የለበሰ አመራሮች በራሳቸው ስለሚተማመኑ ሕዝቡን መልሰው በመልካም አስተዳደር ይገዙታል፣ ከሕዝቡም በብዙ መንገድ ይቀራኛሉ። በተቃራኒ አምባገነኖች ኢሕጋዊ በሆነ መንገድ ስለሚገዙና በራሳቸው ስለማይተማመኑ ከሕዝቡ ይነጠላሉ፣ ሕዝቡንም ያሰቃዩታል፣ ‘በትረ ያፀንዕ ኃይለ መንግሥት’ የሚለውን ዘይቤ/ፈሊጥ ቃል በቃሉ ይተገብሩታል። ጨካኞችም ናቸው። ስየ “ጭካኔ ከፍርሃት ማህፀን የሚወለድ አደገኛ በሽታ ነው” (ገጽ 191) ያለው አማን በአማን የሚያሰኝ ነው።

በገጽ 196 አንድ በጣም የገረመኝ ነገር ደራሲው በሐተታ መልክ አቅርቦታል። ይኸውም የዓድወ ድል መታሰብያ ሐወልት አስመልክቶ ነው። ለመቶኛ ዓመት የአድዋ ድል መታሰብያ “ፕሪዚደንት ነጋሶ ጊዳዳ መሠረት እንዳስቀመጡ ሁሉ፣ አቶ አሊ አብዶም የአዲስ አበባ ከንቲባ በነበሩበት ጊዜ አዲስ አበባ ላይም ቦታ ተመርጦ ፕረዚደንት ነጋሶ ለአድዋ ድል መታሰብያ ሐወልት ግንባታ የመሠረት ድንጋይ አኑረው ነበር” ይልና “አቶ አርከበ ይኸንን ለሀገራችን ታሪክና ለኢትዮጵያውያን ተጋድሎ ትልቅ ፋይዳ ያለውን የመታሰብያ ሐወልት ወደጎን ትቶ ለአድዋ ድል መታሰብያ የታሰበውን አከባቢ ለመንገድ ሥራ አውሎታል፣ ቅያሬ ቦታም ሳይመደብ ቀርቷል” ብሎ ይደመድመዋል።

‘የገረመኝ ነገር’ ያልኩት፡ እንኳንስ ኢትዮጵያውያን ሌሎች አፍሪቃውያንና በየክፍላተ አህጉሮቹ የሚገኙ ጥቁር ሕዝቦች በአድዋ ድል ይኮራሉ። ስለዚህም ጉዳይ በተደጋጋሚ ጽፍያለሁ፣ በ1996 እአአ የዓድወ መቶኛ ዓመት በኢትዮጵያውያን የተዘጋጀ ስብሰባ በሃዋርድ ዩኒቨርሲቲ ተካሂዶ ነበር፣ እኔና ፕሮፌሰር ጆሴፍ ሃሪስ ደግሞ ከተናጋሪዎቹ መሃል ነበርን። የኔ ተራ እንደደረሰ በድንገት በጣም ብዙ ራስ ተፈርያኖች ነጭ የሐበሻ ልብስ ለብሰው፡ የኢትዮጵያ ባንዴራ እያውለበለቡና እዘመሩ ወደ አዳራሹ ገቡ። ጫጫታም ስለበዛ ንግግሬን

ላምስት ደቂቃ ያህል አቋረጥኩት። በዛን ጊዜ ራስ ተፈሪያኖቹ ለኢትዮጵያ ያሳዩተን ፍቅርና ክብር ምን ጊዜም አልረሳውም።

በገጽ 222 ስየ "በምስክርነት ጠርተናቸው አደጋውን እያወቁ ቆመው አውነታውን ለተናገሩት ወገኖቻችን በሙሉ ታላቅ አክብሮት አለኝ፣ እንደቤተሰብም አለን" ይላል። በጣም ጥሩ አባባል ነው! በኔ አመለካከት ግን ስየ ከምያደርገው ምስጋና ባሻገር እርሱ ራሱ እንደገና እንደተፈጠረ ነው የምረዳው፣ ያ ሁሉ ሰቆቃ ባያጋጥመው ኖሮ ምናልባት የሕዝቡንም ብሶት አሁን እንደሚገነዘበው ያህል ላያውቀው ይችል ነበር የሚል ግምት አለኝ፣ ሥልጣኑን እንደ ሕወሐት ብቻ ቢቀጥል ኖሮም ምናልባት አሁን ለሕዝብ ያለው ፍቅር ባልተጎናጸፈና ትሕትናም ባላሳየም ነበር የሚልም ተጨማሪ ግምት አለኝ፣ የመላ-ኢትዮጵያ እምነቱም አንዳሁኑ የጸናበት በዚህ ተመክሮ ካለፈ በኋላ ነው የሚል እምነት አለኝ።

በገጽ 236 ስየ እሱ ተፈቶ ወንድሙ አሰፋ ግን ሳይፈታ ስለቀረና ከእስር ቤት እንዲለቀቅ አንዳንድ የውጭ ዲፕሎማቶች እንደ ደቪድ ክሬመር፡ በአመሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት ኃላፊ፡ ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ጊዜ አነጋግሯቸው እንደነበር ይገልጻል። እሳቸውም በበኩላቸው የኢትዮጵያ ባለሥልጣናትን አነጋገሩና አንድ ሳምንት በልሞላ ጊዜ አሰፋ ተፈታ። የአሰፋ መፈታት መልካም፣ ልክ ስየ አንደተፈታና ከቤተሰቡ ጋር እንደተቀላቀለ ለእናቱ ትልቅ ፀጋ ያስገኘው፡ የወንዱሙ መፈታትም ለጠቅላላ ቤተሰቡ ትልቅ ደስታ እንደሆነ ከደራሲው አጻጻፍ መገንዘብ ይቻላል። ሆኖም ግን ባለሥልጣናቱ ምን ያህል ነጻ እንዳልሆኑና አንዳንዴም አገሪቷን ማን ነው የሚያስተዳድራት ብሎ ለመጠየቅ የሚስገድደን ይሆናል።

ብዙውን ጊዜ እኛ ኢትዮጵያውያን ወደ ፖለቲካ ግዙፍ ዝንባሌ እናሳያለን፣ ባሁኑ ጊዜም ጨዋታችንና ወጋችን ሁሉ ፖለቲካ ሆኗል። ሰብአዊ፡ ኀሊናዊ፡ ሞራለዊ፡ ኃይማኖታዊ (ይህም ፖለቲካ ሆነዋል ለነገሩ) እና ሕብረተሳባዊ ጎኖችንም መዘንጋት የለብንም። ለዚሁ አግባብነት ያለው ታድያ መጽሐፉን ሳነበው በጣም የነካኝና የተናነቀኝ እንዲሁም እምባየ የቋጠረው ደራሲው በገጽ 237 ያሰፈረውን ነው፣ እንዲህ ይላል፡-

"የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ አሰፋ ተፈታ፣ እናታችንም ፊቱን ዳበሰችና "አየችው"፣ ምኞትዋም ተሳካላት። ከዚህ በኋላ ዋናው ጥያቄዋ 'ወደ ቤቴ መልሱኝ፣ አገሬ ይቅበረኝ፣ ቤተክርስትያኔ ውስጥ በሠራሁት የመቃብር ቤት መቀበር እፈልጋለሁ' የሚል ነበር። 'እግዚአብሔር የለመንኩትን መልሶልኛል፣ ልጆቼ መጥታችሁልኛል። ከእንግዲህ እግዚሃርን የምለምነው ሬሳየ ከቤቴ በእናንተ ትከሻ እንዲወጣ እንዲፈቅድ ነው፣ እና መልሱኝ' በማለት መነትነት ያዘች።

እኛም መሄድ እንዳለባት ተስማማን፣ ስለሆነም የስንብት ፕሮግራም አዘጋጀን። በዝያ አጋጣሚም ሁላችንም የአብርሃ ልጆች አዲስ አበባ ውስጥ ነበርን። ልጆቻችን ይዘን አብረናት ዋልን። እያንዳዳችንም ብእጆቿ እየዳበሰች ሳመችን። የልጅ ልጆቿም እንደዚሁ እየዳበሰች ሳመች። እግዚአብሔርን አመሰገነች። ባያዩላትም አይኖችዋን

ገልጣ ሁለት እጆችዋን ወደ ላይ ዘርግታ ማመስገን ዋና ሥራዋ ነበር፣ እግዚአብሔርን ስትለምን የነበረውም ይህን ለማየት ነበርና።

ይህን አድርገን ለማስታወሻ ቪድዮ ቀረፅን፣ ፎቶግራፎችም አነሳን። ማታ ላይ ተሰናበትናት፣ እርሷም ከሚቀጥለው ቀን ጀምሮ መድከም ጀመረች፣ እንቅልፍ ብቻ ሆነች፣ ልጆችዋን እስከታይ ድረስ ተስፋ ሳትቆርጥ እጅዋን ላለመስጠት የታገለችው ሴት ለመሰናበት የወሰነች ይመስል መተኛት ያዘች፣ እየደከመችም ሄደች...አረፈች።"

አሁን ወደ ፖለቲካው ልመልሳችሁና በገጽ 239 ደራሲው "ነጻና ገለልተኛ ዳኝነት የመኖር ወይም ያለመኖር ጉዳይ በአንድ ሃገር ሁለንተናዊ መረጋጋት ላይ ትልቅ ፋይዳ አለው" ይላል፣ ትክክለኛ አነጋገር ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ ግን ከነጻነትና ዳኝነት ጋር መያያዝ ያለባቸው ነገሮች ቢኖሩ አጠቃላይ የአገሪቷ የፖለቲካ መዋቅሮች፣ ተቋሞችና ባህሎች፣ ስነልቦናዊ አመለካከትም ጭምር ናቸው። የተወሳሰቡና የተጥለፈለፉ የሕብረተሰባዊ ግንኙነቶችን በማጤን ትክክለኛ መንገድ እስካልቀየስን ድረስ ደግሞ መሰረታዊ ለውጥና የምንፈልገውን ፍትሐዊ የፖለቲካ ሥርዓት መገንባት አንችልም። መገንባት ከቻልን ግን ስየ በገጽ 241 በንኡስ ርእስ 'ሕገ-መንግሥቱን የመተርጎም ሥልጣን ለፍርድ ቤት መተው አለበት' ያለውን እውን ይሆናል።

ከገጽ 251 እስከ መጨረሻው ገጽ 440 አባሪዎች ስለሆኑ ለአንባቢ ትቼዋቸዋለሁ!

All Rights Reserved. Copyright © IDEA, Inc. 2010 አልትተ ገላውዴዎስ አርአያ። Dr. Ghelawdewos Araia can be contacted for educational and constructive feedback via dr.garaia@africanidea.org